# የዐማራ ክልል መዝሙር ሕገ መንግሥታዊ ትርጉምና ዐውዳዊ ትንተና

መስፍን መሰለ[1]

**አኅጽሮተ ጽሑፍ**

የዐማራ ክልል ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 4 ክልሉ የራሱ መዝሙር እንደሚኖረውና በመዝሙሩ የሚንፀባረቁ ይዘቶችን በመዘርዘር ይደነግጋል፡፡ በድንጋጌው መሠረትም የክልሉን መዝሙር በማዘጋጀት በትምህርት ቤቶችና በሌሎችም መድረኮች አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ ይኹን እንጂ እስከ አኹን ድረስ በመዝሙሩ ላይ ጥናት ባለመደረጉ ይኽንን ጥናት ማካኼድ አስፈላጊ አድርጎታል፡፡ በጥናቱ በዐማራ ክልል ሕገ መንግሥት ስለ ክልሉ መዝሙር የተደነገገው ተተርጉሟል፡፡ የሕገ መንግሥቱን ዓላማዎች፣ የክልሉ ሕዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ጋራ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ ለመኖር ያለውን እምነትና የክልሉን ሕዝብ የወደፊት የጋራ ዕድል ምን ያኽል መዝሙሩ እንዳንፀባረቀ ተመርምሯል፡፡ መዝሙሩ የክልሉንና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕግጋተ መንግሥታት ድንጋጌዎችንና ሌሎች የመረጃ ምንጮችን፣ እንዲኹም የመዝሙሩን ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ዐውዶች መሠረት በማድረግ ተተንትኗል፡፡ ከጥናቱ ውጤት መረዳት እንደተቻለው በመዝሙሩ የሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች በሚገባ አልተንጸባረቁም፡፡ ይኹን እንጂ በመዝሙሩ የክልሉ ሕዝብ ከሌሎች ሕዝቦች ጋራ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ ለመኖር ያለው ፍላጎትና የክልሉ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ወደፊት የተሻለ የጋራ ሕይወት እንዳላቸው ያንፀባርቃል፡፡ መዝሙሩ በአንድ በኩል የኽምራ፣ የአዊ፣ የኦሮሞ ብሔረሰቦችና ሌሎች ሕዝቦች በክልሉ መኖራቸውን ይገልጻል፡፡ በሌላ በኩል ስለ ዐማራ ክብር ብቻ ይቀሰቅሳል፡፡ በዚኽም በብሔረሰብ አስተዳደሮች ነዋሪዎች ቅሬታ ፈጥሯል፡፡ ከዚኽም በላይ የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ተማሪዎቹ መዝሙሩን መዘመራቸውን እንዲያቆሙ አድርጓቸዋል፡፡ እንዲኹም የት? መቼ? እና እንዴት? እንደሚዘመር በዝርዝር ሕግ ባለመደንገጉ፣ መዝሙሩ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ አንድ ወጥ የኾነ አገልግሎት አይሰጥም፡፡ ይኽም ኹኔታ መዝሙሩ የክልላዊም፣ የሀገራዊም አንድነትን ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት በሚፈለገው መልኩ እንዲያግዝ አልተደረገም፡፡

<u>ቁልፍ ቃላት</u>፡- [የዐማራ ክልል፣ ሕገ መንግሥት፣ መዝሙር፣ ዴሞክራሲ፣ የጋራ ዕድል፣ ብሔር/ብሔረሰብ/ሕዝብ]

## 1) መግቢያ እና ዐውዳዊ ዳራ

በዐማራ ክልል ሕገ መንግሥት አንቀጽ 2 እንደተደነገገው “የአማራ ብሔራዊ ክልል[2] በሰሜን የትግራይ ክልል፣ በምሥራቅ የአፋር ክልል፣ በደቡብ የኦሮሚያ ክልል፣ በምዕራብ የቤኒሻንጉል

[1] በዐድስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ የፎክሎርና ሥነጽሑፍ ተመራማሪ፡፡

[2] በዐማራ ክልል ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፩ የክልሉ መጠሪያ “የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት” መኾኑ ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 (3) “የአማራ ክልል” በሚል መጠሪያ የፌዴራሉ መንግሥት አባል መኾኑ ተደንግጓል፡፡ በዚኽ ጥናታዊ ጽሑፍ

(ጉሙዝ) ክልልና ሱዳን ያዋስኑታል።"[3] በክልሉ ካሉት ዐሥራ ኹለት የዞን አስተዳደሮች መካከል ሦስቱ (የኽምራ፣ የአዊና የኦሮሞ) የብሔረሰብ የዞን አስተዳደሮች ናቸው። የአርጎባና የቅማንት ብሔረሰቦችም ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳደሩ ወረዳዎች መኾናቸው በዐዋጅ ተደንግጓል።

ከ1983 ዓ. ም. ጀምሮ ክልሉን በበላይነት የሚመራው የቀድሞው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢሕዴን) በኋላ የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) የአኹኑ "የአማራ ብልጽግና ፓርቲ" ነው። የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢሕዴን) መሥራቾች ከኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ/ሠራዊት (ኢሕአፓ/ሠ) አፈንግጠው የትግራይ ሕዝብ ነጻነት ግንባር (ትሕነግ) ይቆጣጠረው ወደ ነበረው ተንቤን አውራጃ ልዩ ስሙ ተከራርዋ ወደ ተባለው ቦታ የኼዱ ናቸው። እነሱም ኅዳር 11 ቀን፣ 1973 ዓ. ም. የፖለቲካ ድርጅቱን መሠረቱ። ኢሕዴን በጊዜው ለመታገል የተነሣው በኢትዮጵያ ሰፍኖ የነበረውን መንግሥታዊ ካፒታሊዝምንና ሁሉም ዓይነት ኢምፔሪያሊዝምን እንዲሁም ሙሉ በሙሉ ያልተንኮታኮተውን ፊውዳሊዝምን በር። ስታራቴጂያዊ ግቡም ሕዝባዊ ዲሞክራሲዊ አብዮትን በመምራት ለድል ለመብቃት የሚያስችለውን የላብ አደር ፓርቲ እንዲመሠረት የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ ነበር። በመተዳደሪያ ደንቡ እንደገለጸው ኢሕዴን ኅብረ-ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት ነው። አታጋይ ድርጅት ያላገኙ የተለያዩ ብሔር-ብሔረሰቦች ተወላጆችን በአባልነት የሚያሰባስብ፣ በመደብ ጥያቄ እንጂ "በአንድ ብሔረሰብ የብሔራዊ እኩልነት ጥያቄ ዙሪያ" (የብአዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት፣ 2008፤ 73) የተደራጀ አልነበረም።

የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሚክራሲያዊ ንቅናቄ በፖለቲካ ፕሮግራሙና በመተዳደሪያ ደንቡ ያፀደቀውን ከግብ ለማድረስ የተራዘመ የገጠር የትጥቅ ትግል ማካኼድ ቀጠለ። በመጀመሪያ ከትግራይ ሕዝብ ነጻነት ግንባር፣ ቀጥሎም ከኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦሕዴድ) ጋር ግንባር በመፍጠር የኢትዮጵያን መንግሥት በትጥቅ ትግል በማዳከም ግንቦት 20 ቀን፣ 1983 ዓ. ም. ለሥልጣን በቃ። "በሰኔ ወር 1983 ዓ. ም. የሽግግር መንግሥት ለመመሥረት በተጠራው ጉባዔም ኢሕዴን ስምንት ወንበሮችን በመያዝ የሽግግሩ መንግሥት መሥራች አባል ለመሆን ችሏል" (የብአዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት፣ 2008፤ 148)።[4] ኢሕዴን በ1985 ዓ. ም. "በአማራ

---

የተመረጠው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት "የአማራ ክልል" በማለት የጠራበትን ክልል የሚለውን ስም ነው።

[3]"የቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት ዐዋጅ ቁጥር 1/1988" አንጽ 2 የብሔራዊ ክልሉ ወሰን በሰሜን የትግራይ ክልል ማኾኑን ይደነግግ ነበር። ኾኖም "ተሻሽሎ የወጣውን የቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት ማጽደቂያ ዐዋጅ ቁጥር 31/1995" ብሔራዊ ክልሉ በሰሜን በኩል የሚዋሰነው ከየዐማራ ክልል ጋር መኾኑን ይደነግጋል። ተሻሽሎ የወጣው የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት ማጸደቂያ ዐዋጅ ቁጥር 45/1994 አንቀጽ 2 ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል እንደሚዋሰን አይደነግግም።

[4]ብሔራዊ ክልላዊ የሽግግር መስተዳድሮችን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 7/1984 አንቀጽ 3 (1) ስድሳ ሦስት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች በዐሥራ አራት ብሔራዊ ክልል መስተዳድሮች ሥር እንደሚገኙ ተደንግጓል። ይኽ ቁጥር በተራ ቁጥር 8 በክልል ሦስት ቃሉ አካባቢ የሚገኙ የኦሮሞ ብሔር አባላትንና በተራ ቁጥር 65 የተገለጸውን አዲስ አበባን አይጨምርም። በተጠቀሰው ዐዋጅ አንቀጽ 3 (2) (ሀ) ሳሆና ኩናማ በክልል አንድ፣ ኮማ [ኮሞ]፣ ሰሜን ማኦ [ማኦ] እና ሽናሻ በክልል ስድስት፣ ዘይሴ፣ ጎበዝ [ጎበዜ] ጊዶሌ፣ በክልል ዘጠኝ፣ አርቦሬ [ኤርቦሬ]፣ ኛንጋቶም፣ ፀማይ፣ ዲመ [ዲሜ]፣ ቦዲ [ቦዴ]፣ በክልል ዐሥር፣ ኖአ [ናኢ]፣ ዘልማሞ፣ ሚኒት [መእኒት] እና ሸኮ በክልል ዐሥራ አንድ ሥር እንደሚገኙ ዕውቅና ቢሰጥም በወረዳ ደረጃ አስተዳደር መመሥረት እንደማይችሉ ተደንግጓል። በተለያዩ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድሮች የሚኖሩት የዐማራ ብሔር ተወላጆች በቃሉ አካባቢ

ክልል የሚገኙትን የዐማራን፣ የኸምራን፣ የአዊንና የኦሮሞን ሕዝቦች በመምራት የዐማራ ብሔራዊ ክልላዊ የሽግግር መንግሥትን መሠረተ" (የብአዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት፣ 2008፤ 150)፡፡

የፖለቲካ ድርጅቱ ሲመሠረት ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮትን መርቶ ለድል ለሙብቃትና የላብ አደር ፓርቲ ለመመሥረት የሚያደርገውን ትግል ትቶ ጥር 17 ቀን 1986 ዓ. ም. ለዐማራ ሕዝብ ለመታገል ወሰነ ፡፡ የፖለቲካ ድርጅቱን መጠሪያም ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) እንዲኾን ተስማማ፡፡ ከዐሥራ ሦስት ዓመት በፊት ኢሕዴን ሲመሠረት ያፀደቀውንና ሲታገልለት የነበረውን ፕሮግራም በመተው ለዐማራ ሕዝብ ለመታገል ወሰነ፡፡ ይኽን የወሰነበብት ምክንያት፡- አንደኛ፣ ጠባቦች የዐማራውን ሕዝብ ጨቋኛቸውና በዳያቸው አድርገው መቁጠራቸውን ለመታገልና የዐማራውን ሕዝብ ጥቅሞች ለማስከበር ነው፡፡ ኹለተኛ፣ በአንድ በኩል ትምክህተኞች "የአማራው ሕዝብ የራሱ ድርጅት ስለሌለው ጥቃት ደረሰበት" በማለት የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅትን (መዐሕድ) መመሥረታቸው፣ በሌላ በኩል "አማራ የሚባል ሕዝብ የለም" በማለት በዐማራው ላይ የከፈቱትን ዘመቻ ለመታገል ነው፡፡ ሦስተኛ፣ ትምክህት ያልተጠናወተውን፣ ገዢ መደብም፣ ነፍጠኛም ያልኾነውን "የሰፊውን የዐማራ ሕዝብ" ጥቅም በሀገሪቱ በተፈጠረው የሰላምና የዲሞክራሲ መድረክ (በሽግግሩ መንግሥት) ጥቅሙን ለማስከበር ነው፡፡ አራተኛ፣ ኢሕዴን ከ1973 ዓ. ም. እስከ 1983 ዓ. ም. ባደረገው የትጥቅ ትግል በስፋት የተንቀሳቀሰው የዐማራው ሕዝብ በሚኖርበት አካባቢ፣ የታገለውና በስፋት ያታገለው የዐማራውን ሕዝብ በመኾኑ ነው፡፡ ዐምስተኛ፣ በ1983 ዓ. ም. የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ሲቋቋም ኢሕዴን የሽግግር መንግሥት እስኪቋቋም ክልሉን በመምራቱ ነው፡፡ ይኸም ኢሕዴን ለዐማራ ሕዝብ በግንባር ቀደምነት ለመታገል በመንቀሳቀስ በ1985 ዓ. ም. በክልሉ የሚገኙትን የዐማራን፣ የኸምራን፣ የአዊንና የኦሮሞን "ሕዝቦች" በመምራት የክልሉን የሽግግር መንግሥት በመመሥረት መምራት በመቻሉ ነው (የብአዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት፣ 2008፤ 148-149)፡፡

በተጠቀሱት ምክንያቶች "ኢህዲን ኅብረ-ብሔራዊ አደረጃጀቱን በመቀየርና የዐማራ ብሔራዊ ድርጅት ሆኖ መደራጀት እንዳለበት ወሰነ፡፡ ...ከጥር 12 እስከ 17/1986 ዓ. ም. በባህር ዳር ከተማ በተካሄደው ሦስተኛው ድርጅታዊ ጉባዔ የኢህዴን አደረጃጀት ወደ ዐማራ ብሔር ብሔራዊ አደረጃጀት እንዲቀየር ተወሰነ" (የብአዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት፣ 2008፤ 152)፡፡ ኢሕዴን ወደ ብአዴንነት ከተቀየረባቸው ምክንያቶች ይበልጥ ትኩረት የሚሰጡት የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት (መዐሕድ) በመመሥረቱ እሱን መመከት አስፈላጊ ነው ተብሎ መወሰኑን ነው፡፡ ይኽ ባይኾን ኖሮ ኦሕዴድና የሰምጥ ሸለቆ ታጋዮች ማኅበር ከ1983 ዓ. ም. በፊት በረሃ ላይ ሲመሠርቱ የዐማራን ድርጅትም ማደራጀት ይቻል ነበር፡፡ በኋላም በሽግግሩ መንግሥት የዐማራ ተወካይ

---

እንደሚኖሩት የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች ዕውቅና አልተሰጣቸውም፡፡ እንደዚኹም በክልል ስድስት ለሚኖረው የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች ዕውቅና አልተሰጠም፡፡ በክልል *ዐሥራ ሦስት* የሚኖረው የዐማራ ብሔር ተወላጅ ቁጥር ከሐረሪ ሕዝብ ቢበልጥም በሽግግሩ መንግሥት የክልሉ ባለቤት የሐረሪ ሕዝብ እንደኾነ ተደንግጓል፡፡ በክልል *ዐሥራ ሦስትም* (ሐረርማ)፣ በክልል *ዐሥራ አራትም* (አዲስ አበባ ከተማ) የሚኖረው የኦሮሞ ልዩ ብሔራዊ ጥቅምና የፖለቲካ መብት እንደሚጠበቅለት በአንቀጽ 3 (4) ተደንግጓል፡፡ የክልል ዓሥራ ሦስት (የሐረር ከተማ) እና የክልል *ዐሥራ አራት* (አዲስ አበባ ከተማ) ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድሮች ተጠሪነት ለማዕከላዊ የሽግግር መንግሥት እንዲኾን ተደንግጓል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 416/1996 የተቋቋመው የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር (የድሬ ዳዋ ከተማ) በአዋጅ ቁጥር 7/1984 ራሱን የቻለ ክልል ወይም በሌላ ክልል ሥር መኾኑ አልተደነገገም፡፡

አለመኖር እንደታየ በ1983 ዓ. ም. መመሥረት ይቻል ነበር፡፡ ከ1983 ዓ. ም. በፊት ወይም በሽግግሩ ዘመን የዐማራን ሕዝብ የሚመራ የፖለቲካ ድርጅት አለመመሥረቱ "አስቸጋሪው የሽግግር ወቅት እስኪጠናቀቅ ድረስ ዐማራን ከመድረኩ ገለል አድርጎ ማቆየት ይሻላል በሚል እምነት ሆን ተብሎና ታስቦበት የተሠራ" ነው (ቹቹ፣ 2011፤ 176)፡፡ ክልሉን በበላይነት የመምራት ኃላፊነት የወሰደው ኢሕዴን/ብአዴን በመጀመሪያው ምርጫ ክልሉን በብቸኝነት ለመምራት መመረጡን ራሱ አረጋገጠ፡፡

"በሕዝብ ተመርጫለኹ ያለው" ኢህዴን/ብአዴን የዐማራን ሕዝብ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲኹም የኢኮኖሚ ጥቅሞች አላስከበረም፡፡ ይልቁንም የዐማራን ሕዝብ እያጠቃና እያስጠቃ ክልሉን በብቸኝነት መምራቱን ቀጠለ፡፡ ይኽን በተመለከተ ቹቹ (2011፤ 180) "ብአዴን እስከ 2010 ዓ. ም. ድረስ ዐማራን ያጠቃና ያስጠቃ፣ የዐማራን ሕዝብ ለጠላቶቹ አሳልፎ የሰጠ፣ ከልቡ ዐማራ ሳይሆን ዐማራነትን ተላብሶ በዐማራ ሕዝብ ላይ ያላገጠ፣ የራሱ ማንነት ያልነበረው፣ የህወሓትን ሥነ ልቡና ተላብሶ የከረመ "ቀሽም ድርጅት" ነበር ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡"[5] በማለት ይገልጻሉ፡፡ እንዲኽ ዓይነት ቁመና የነበረው ኢሕዴን/ብአዴን የዐማራነትን ክብር ከፍ የሚያደርግ መዝሙር እንዲዘጋጅ በሕገ መንግሥቱ ደነገገ፡፡

በ1988 ዓ. ም. ለመጀመሪያ ጊዜ ባጸደቀው የክልሉ ሕገ መንግሥት ክልሉ መዝሙር እንደሚኖረውና ምን ምን ማንፀባረቅ እንዳለበት ደነገገ፡፡ የክልሉን መዝሙር በ1989 ዓ. ም. በማውጣት በትምህርት ቤቶችና በክልል ጉባዔዎች ማዘመር ቀጠለ፡፡ በዐማራ ክልል ሕገ መንግሥት ስለ ክልሉ መዝሙር የተደነገገውን የተረጎመ፣ በመዝሙሩ እንዲንፀባረቅ የተደነገገውን የመረመረ፣ መዝሙሩን ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ዐውዶችን መሠረት በማድረግ የተነተነ ጥናት ባለመኖሩ ይኽን ጥናት ማካኼድ አስፈላጊ ኾኗል፡፡

---

[5] ኢህዴን/ብአዴን ከ2010 ዓ. ም. በፊት በዐማራ ሕዝብ ላይ ያደረሰውንና እንዲደርስበት ያደረገውን ጥቃት በማረም ወደ እውነተኛ የዐማራ ድርጅትነት ለመሸጋገር ጥረት እያደረገ እንደኾነ ቹቹ ያምናሉ፡፡ እምነታቸውንም ሌሎች እንደሚጋሯቸው "…በአዴን ለዐማራ ሕዝብ በአጋጣሚ የተገኘ ድርጅት፣ የህወሓትን ዓላማ በዐማራ ክልል ለማሳካት የተጋ፣ በሂደት ደግሞ ከህወሓት ጫና በመላቀቅ ወደ እውነተኛ ዐማራዊ ድርጅትነት ለመሸጋገር ጥረት እያደረገ ያለ ድርጅት ተብሎ ቢፈረጅ ብዙውን ሰው ሊያስማማ ይችላል ብዬ  አምናለሁ፡፡" (ቹቹ፣ 2011፤ 181) በማለት ይገልጻሉ፡፡  ቹቹ በማጠቃለያቸው  ብዙው ሰው እንደሚስማማ ለማመን የቻሉበትን ግንዛቤ ለመጋራት የድርጅቱን የትግል እንቅስቃሴ በቅርበት መረዳትን ይጠይቃል፡፡ ከዚኽም በላይ፣ ከእሳቸው በተቃራኒ ኢህዴን/ብአዴን/አዴፓ/ብልጽግና ስሙን ከመለዋወጥ በስተቀር ዛሬም "ለንጉሡ አጎንብሱ" በሚል ብሂል የሚመራ የፖለቲካ ድርጅት አድርገው የሚገልጹት አሉ፡፡ ማስረጃቸውም ከ2010 ዓ. ም. በኋላም ያለፍላጎቱ በትግራይ ክልል ሥር እንዲጠቃለል በተደረገው ዐማራ ላይ ህወሓት የበደል ዓይነት ሲያፈራርቅበት ሊታደገው አልሞከረም፡፡ የማይካድራው ጭፍጨፋ የደረሰው በደል የሚደርስበትን ሕዝብ አቤቱታ የሚሰማና መፍትኼ የሚሰጥ በመጥፋቱ ነው፡፡ በመተከል፣ በኦሮሚያና በደቡብ ክልሎች በዐማራው ላይ የሚፈጸምበትን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥሰት አልከላከለም፡፡ በመተከል የዐማራና የአገው ተወላጆች ተደጋጋሚ ጥቃት የተፈጸመባቸውና በጅምላ የተቀበሩት ከ2010 ዓ. ም. ለውጥ በኋላ ነው፡፡ በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተሞች እንዲሁም በሐረሪ ሕዝብ ክልል ዐማራው የሚደርስበትን መገለል ለማስቀረት የሚያደርገው ጥረት ለመኖሩ የተጨበጠ ማስረጃ የለም፡፡ ጉደለት አለበት የሚባለው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የሚፈቅደውን መብት በየክልሎቹ ሕገ መንግሥት ዐማራው ተከልክሎ ዛሬም ምርጫ ለማድረግ የሚደረገው ዝግጅት ከ2010 ዓ. ም. በፊት የነበረውን ኹኔታ የሚያስቀጥል ነው፡፡ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሳይደረግ ምርጫ እንዲደረግ መተባበር ኢፍትሓዊ የበጀት ድልድል እንዲቀጥል መስማማት ነው፡፡

የዚኽ ጥናት ዋና ዓላማ የዐማራን ክልል መዝሙር መተርጎምና መተንተን ነው፡፡ ከዚኽ ዐቢይ ዓላማ የሚመነጩ ዝርዝር ዓላማዎች፡- አንደኛ፣ በዐማራ ክልል ሕገ መንግሥት አንቀጽ 4 በክልሉ መዝሙር እንዲንፀባረቁ የተደነገጉትን የክልሉን ሕገ መንግሥት ዓላማዎች፣ የክልሉ "ሕዝብ" ከሌሎች የኢትዮጵያ "ሕዝቦች" ጋር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ ለመኖር ያለውን እምነትና የክልሉን "ሕዝቦች" የወደፊት የጋራ ዕድል የሚሉትን መተርጎም፤ ኹለተኛ፣ በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 4 የተደነገጉት በመዝሙሩ ምን ያኽል እንደተንጸባረቁ መርመር፤ ሦስተኛ፣ ስለክልሉ መዝሙር የተደነገገውን የክልሉን ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ዐውዶች መሠረት በማድረግ መተንተን የሚሉት ናቸው፡፡ እነዚኽን ዓላማዎች ለማሳካት ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፡- የዐማራ ክልል ሕገ መንግሥት ስለ ክልሉ መዝሙር የደነገገው ትርጉም ምንድን ነው? በክልሉ ሕገ መንግሥት በመዝሙሩ እንዲንጸባረቁ የተደነገጉት ምን ያኽል ተንጸባርቀዋል? ስለመዝሙሩ የተደነገገው ከክልሉ ፖለቲካዊ፣ ታሪካዊና ማኅበራዊ እውነታዎች ጋር ምን ያኽል ይጣጣማል? የሚሉት ናቸው፡፡

የዚኽ ጥናት የመረጃ ምንጮች የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት፣ የዐማራ ክልል ሕገ መንንግሥት፣ የክልሉ መዝሙር፣ የተለያዩ ዐዋጆች፣ የኢሕዴን/ብአዴን የፖለቲካ ፕሮግራሞች፣ የታሪክ ጽሑፎች፣ መጽሔቶችና ጋዜጦች ናቸው፡፡ በቃለ መጠይቅ የተገኘን መረጃም ተጠቅመናል፡፡ መዝሙሩ የተተረጎመውና የተተነተነው የተደረሰበትን ዐውድ መሠረት በማድረግና ገላጭ የትንተና ዘዴን በመጠቀም ነው፡፡

በፌዴራል ሥርዓት የሚመራ ሀገር ውስጥ የአንድ ክልላዊ መንግሥት የራሱ መዝሙር እንዳለው የሚገልጽ መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ ይሁን እንጅ፣ የዐማራ ክልል መዝሙር በትምህርት ቤቶች የክልሉ ሰንደቅ ዓላማ ሲወጣና በክልሉ ከፍተኛ ፖለቲካዊ ትርጉም በሚሰጣቸው ስብሰባዎች ላይ እንዲዘመር ታስቦ መዘጋጀቱ፣ ከአንድ ሀገር ብሔራዊ መዝሙር ጋር ተመሳሳይ ተግባር አለው ማለት ይቻላል፡፡ ብሔራዊ መዝሙር የሀገሪቱ ዜጎች በየዕለቱ ብሔራዊ ማንነታቸውን የሚገነዘቡበት ትእምርት ነው (Butz, 2009)፡፡ ቡትዝ አከለውም የአንድ ሀገር ትእምርቶች (ለምሳሌ፣ ሰንደቅ ዓላማዎች፣ አርማዎች፣ ብሔራዊ መዝሙሮች) ሕዝቦች ከሀገራቸው ጋር የሚኖራቸውን ሥነ ልቡናዊ ትስስር ይጨምራሉ፡፡ ስለኾነም፣ ብሔራዊ መዝሙሮች በዘማሪዎቹ ቡድኖች መካከል የጋራ ስሜት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ ተብሎ ያታመናል (Daughtry, 2003)፡፡ የዐማራ ክልል የክልሉን መዝሙር ሲያዘጋጅ የተጠቀሱትን የብሔራዊ መዝሙር ተግባሮች ታሳቢ ያደርጋል ተብሎ ያታመናል፡፡

ስለኾነም የየክልሉ መንግሥት መዝሙሩን የደረሰበት ዋና ዋና ዓላማዎች አንደኛ፣ የክልሉ ሕዝብ አንድ የጋራ ትእምርት እንዲኖረውና "የእኔ" ብሎ እንዲቀበለውና የክልሉን ሕዝብ አንድነት ማጎልበት ነው፡፡ መዝሙሩ ይኽን ዓላማ የሚያሳካው ትእምርቱ ሕዝብ የሚቀበለውንና የሚያምንበትን፣ ታሪኩን፣ ቅርሱን፣ ባህሉንና የተፈጥሮ ሀብቱን ሲያንፀባርቅ ነው፡፡ በሕዝቡ ማንነት ላይ የተመሠረተ ይዘት ያለው፣ ትናንት ያለፈበትን፣ ዛሬ የሚገኝበትንና ወደፊት ሊደርስበት የሚያስበውንና የሚፈልገውን እሴነቱን በትክክል ሲገልጽ ነው፡፡ መዝሙሩ ካለፈ ታሪኩ የተነጠለ፣ ማንነቱን የማይገልጽና የማያስከብር፣ ዛሬ የቆመበትንና የወደፊት ተስፋውን

የማይገልጽ ከኾነ የተፈለገውን ውጤት አያስገኝም፡፡ ኹለተኛ፣ የመዝሙሩ ዓላማ የክልሉ ሕዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጋር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ላይ በመመሥረት ትብብርንና አንድነትን ማጠናከር ነው፡፡ ይኸ ዓላማ የሚሳካው በክልሉ የሚኖሩ የዐማራ፣ የኽምራ፣ የአዊ፣ የኦሮሞ፣ የአርጎባና የቅማንት ብሔረሰቦች፣ እንዲኹም ሌሎች ሕዝቦች በሌሎች ክልሎች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸው መከበራቸው ሲረጋገጥ ነው፡፡ ይኸ ካልኾነ መዝሙሩ በትምህርት ቤቶችና በጉባዔዎች መዘሙሩ በራሱ የሚፈለገውን ዓላማ አያሳካም፡፡ መዝሙሩ እንዲዘጋጅ ያደረገው የዐማራ ክልል መንግሥት ምን ያኽል ዓላማውን እንዳሳካበት ለመረዳት በሕገ መንግሥቱ የተደነገገውን መሠረተ ሐሳብ መዝሙሩ በትክክል ማንፀባረቁንና አለማንፀባረቁን፣ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ እውነታዎች መግለጻቸውን መተንተን አስፈላጊ ነው፡፡ በቅድሚያ የክልሉን መዝሙር ለማዘጋጀት የተደረገውንም እንቅስቃሴ ኺደት እንደሚከተለው እንመረምራለን፡፡

የዐማራ ክልል መዝሙር የተዘጋጀው የክልሉ ምክር ቤት ባቋቋመው አስተባባሪ ኮሚቴ አማካኝነት ነው፡፡ ዝግጅቱም በተለያዩ የሥራ ተግባሮች ተከናውነዋል፡፡ “የክልሉ ምክር ቤት በ2ኛው መደበኛ ጉባኤው ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የክልሉን የሕዝብ መዝሙር አዘጋጅቶ እንዲያቀርብ” ኀላፊነት ሰጠ (የአማራ ብሔራዊ ክልል መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ 1985፣- 1992)፡፡ በዚኹ መሠረት የሥራ አስፈጻሚው ለክልሉ መዝሙር የሚኾን ግጥም ባለሙያዎች እንዲያቀርቡ በመጋበዝ አወዳድሮ የሚመርጥ የመዝሙር ዝግጅት ኮሚቴ አቋቋመ፡፡ ኮሚቴውም ባለሙያዎች ግጥም በማቅረብ እንዲሳተፉ በጋዜጦች ላይ ደጋግሞ ማስታወቂያ በማውጣትና በግልም ግለሰቦችን በማነጋገር በርካታ ግጥሞችን ተቀበለ፡፡ ከተረከባቸው ግጥሞች መካከል የተሻሉ የሚላቸውን መርጧል፡፡ የዝግጅት ኮሚቴው መዝሙሩን ለማዘጋጀት ያከናወናቸው ዝርዝር ተግባሮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

> የክልሉ ሕዝብ መዘሙር አጠቃላይ ዝግጅት የተከናወነው ክልሉ በአቋቋመው አምስት አባላት ያሉት አስተባባሪ ኰሚቴ ነው፡፡ የዝግጅት ሥራውም ሶስት ዓብይ ምዕራፎችን ያለፈ ሲሆን የመጀመሪያው ምዕራፍ ለመዝሙር የሚሆነውን ግጥም የማዘጋጀት ስራ ነው፡፡ ኹለተኛው ምዕራፍ ለተመረጠው ግጥም ዜማ የማዘጋጀት ስራ ሲሆን የመጨረሻው ምዕራፍ ደግሞ ለግጥሙ የተመረጠውን ዜማ ደረጃውን በጠበቀ አ[ኦ]ርኬስትራና ስቱድዮ እንደገና ተስተካክሎ እንዲቀረጽ ማድረግ ነው፡፡
>
> በመጀመሪያው ምዕራፍ የዝግጅት ኰሚቴው በመዝሙር ግጥም ውድድር ማስታወቂያ ካሰባሰባቸው ግጥሞች መስፈርቱን ያሟሉ ብሎ በደረጃ መርጦ ያቀረባቸውን ሥራ አስፈጻሚ ኰሚቴው ለ3ኛው መደበኛ ጉባኤ አቅርቦ ም/ቤቱ እንዲመክርበትና ውሳኔ እንዲሰጥበት አድርጓል (የአማራ ብሔራዊ ክልል መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ 1985 - 1992፤ 13)፡፡

የመዝሙር ዝግጅት ኮሚቴው ከቀረቡለት ግጥሞች አራቱን መርጦ ለ3ኛው መደበኛ ጉባኤ ለውሳኔ አቀረበ፡፡ ኮሚቴው ግጥሞችን የመረጠው "የክልሉን ህዝብ ባህል፣ ታሪክና የተፈጥሮ ሀብት፣ ክልሉ ከሌላው ክልል ህዝብ ጋር በሰላም አብሮ ለመኖር ያለውን ፍላጎት የሚያሳዩ ሥራ ወዳድነቱንና ጀግንነቱን የሚያንጸባርቁ በክልሉ ውስጥ ያሉ ብሔረሰቦችን አንድነትና እኩልነት የሚገልጹ፣ የቃላት አጠቃቀማቸው ህጸናት[ን]ና ሽማግሌዎችን የማያነቅፉ፣ ባሰነኛኘታቸው ለመዝሙር የተመቻቹ ያላቸውን" ነው (የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጉባኤ ምጥን ቃለ ጉባዔዎች፣ 1987-1992፤ 24)፡፡ ምክር ቤቱ "የክልሉን ብሔራዊ መዝሙር ግጥም ማጽደቅ" በሚል የውይይት ርእስ ተመርጠው ለውሳኔ ከቀረቡት አራት ግጥሞች መካከል አንደኛ የነበረውን ከማሻሻያ ሐሣቦች ጋር መርጦ አፀደቀ፡፡ በመዝሙር አዘጋጅ ኮሚቴው አንደኛ ኾኖ የተመረጠውና ጉባዔው ከማሻሻያ ጋር ያፀደቀው ግጥም የሚከተለው ነው፡፡

ባህል ታሪካችን - ሀብታችን የሰፋ፣
በሥራ እናድጋለን - አለን ብሩኅ ተስፋ፡፡

ሰላም እኩልነት - አንድነትን ይዞ፣
በጀግኖች ደም ፈክቷል - የድላችን ጉዞ፡፡
በአኩሪው ተጋድሏችን - ታሪክ ልንሠራ፣
ከኹሉም ሕዝቦች ጋር - ቆመናል በጋራ፡፡

የአማራነትን ክብር - ደማቅ ዐርማ ይዘን፣
ከሌሎች ሕዝቦች ጋር - አብረን እንኖራለን፡፡

3ኛው የክልሉ መደበኛ ጉባዔም በሰጠው የማሻሻያ ሐሳብ መሠረት ለግጥሙ ዜማ እንዲወጣለት የማድረጉንና የመጨረሻ ዝግጅቱን እንዲያስፈጽም ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ኀላፊነቱን ሰጠ፡፡ ለመዝሙር የተመረጠውን ግጥም የዝግጅት በኰሚቴው እንዲስተካከል አደረገ፡፡ ከዚኽ በኋላ የመዝሙሩ አዘጋጅ ኰሚቴ የዜማ ዝግጅት ሥራ እንዲሠራ የብአዴን ሥራ አስፈጻሚ ኰሚቴ መመሪያ ሰጠ፡፡ በዚኹ መሠረትም አዘጋጅ ኮሚቴው ወደ ቀጣዩ ሥራ ተሸጋገረ (የአማራ ብሔራዊ ክልል መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ 1985 - 1992፤ 13)፡፡ ኰሚቴው የዜማ ውድድር ማስታወቂያ በማውጣት የዜማ ሥራዎች በካሴት ወይም በድምፅ ተቀርፀውና በዜማ ምልክት (ኖታ) በጽሑፍ ተዘጋጅተው ቀረቡ፡፡ ሥራዎቹም የሙዚቃ ቅንብር ባለሙያዎች ድጋፍና የውሳኔ መነሻ ሐሳብ በመታገዝ ከቀረቡት ሥራዎች ውስጥ የተሻለውን ዜማ መረጠ፡፡ ግጥሙንና የተመረጠውን ዜማ በአንድነት አዋሕዶ ሥራ ላይ ለመዋል የሚያበቃውን ቅርፅ እንዲይዝ ለማድረግ፣ ማስተካከያ ከተደረገ በኋላ በኦርኬስትራና ስቱዲዮ ተቀርጾ የመጨረሻ መልኩን ይዞ ወጣ፡፡ መዝሙሩም ከነሐሴ 1989 ዓ. ም. ጀምሮ በይፋ ሥራ ላይ እንዲውል ተደረገ (የአማራ ብሔራዊ ክልል መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ 1985-1992)፡፡ ለክልሉ ሕዝብ መዝሙር እንዲኾን በክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኰሚቴ የተመረጠው ግጥም ቀጥሎ የተጠቀሰው ነው፡፡

(1) የታታሪ ሕዝቦች - የታሪክ ማኅደር፣
(2) የአኩሪ ባህል አምባ - የድንግል አፈር፡፡
(3) የሕዝቦችሽ ተስፋ - ለሟ ክልላችን፣
(4) በሰላም በፍትሕ - በልማት ጉዟችን፣
(5) ተባብረን በሥራ - እንከባሻለን፡፡
(6) የአማራነትን ክብር - ደማቅ አርማ ይዘን፣
(7) ከሌሎች ሕዝቦች ጋር - እኩል ተከባብረን፣
(8) በፍቅር በአንድነት - አብረን እንዘልቃለን፡፡

በመዝሙሩ የተንፀባረቁትን የሕገ መንግሥቱን ድንጋጌዎች ለመረዳት ስለ ክልሉ መዝሙር የተደነገገውን መሠረት አድርገን እንመረምራለን፡፡

## 2) የዐማራ ክልል መዝሙር ትርጉምና ዐውዳዊ ትንተና

በዚኽ ክፍል የዐማራ ክልል ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 4 “የአማራ ብሔራዊ ክልል የራሱ መዝሙር ይኖረዋል፡፡ የክልሉ መዝሙር የሕገ-መንግሥቱን ዓላማዎች፣ የክልሉ ሕዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋራ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ ለመኖር ያለውን እምነት እና የክልሉን ሕዝብ የወደፊት የጋራ ዕድል የሚያንፀባርቅ ሆኖ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡” በማለት የደነገገውን በመዝሙሩ መንፀባረቁን እና/ወይም አለመንፀባረቁን እንመረምራለን፡፡ በዚኽ ድንጋጌ የተነሡትን ሦስት ጉዳዮች በንዑስ ርእሶች በመከፋፈል እንመረምራለን፤ እንተነትናለን፡፡ በቅድሚያ በክልሉ መዝሙር እንዲንፀባረቁ የተባሉትን የሕገ መንግሥቱን ዓላማዎች እንመለከታለን፡፡

### 2. 1) የሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች በመዝሙሩ መንንፀባረቃቸው እና/ወይም አለመንፀባረቃቸው

የዐማራ ክልል ሕገ መንግሥት ዓላማዎች በሕገ መንግሥቱ አንድ ባንድ ተለይተው አልተዘረዘሩም፡፡ ይኹን እንጂ፣ በክልሉ ሕገ መንግሥት መግቢያ የተገለጹትንና በተለያዩ አንቀጾች የተደነገጉትን በመመርመር ዓላማዎችን እናስረዳለን፡፡ የዐማራ ክልል ሕገ መንግሥት ዓላማዎች የሕግ የበላይነትን (ፍትሕን) ማስፈን፣ የክልሉን ሕዝብ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች[6] ማስከበር፣ የክልሉን ሕዝብ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት ማፋጠን፣ የብሔር-ብሔረሰቦችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ማክበር፣ በክልሉ ዘላቂ ሰላም ማስፈን፣ እኩልነትንና አንድነትን ማረጋገጥ የሚሉት መኾናቸው በክልሉ ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ ተገልጸዋል፡፡ እነዚኽና ሌሎችም የሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች በክልሉ ሕገ መንግሥት በተለያዩ አንቀጾች ተደንግገዋል፡፡ ትርጉማቸውን በአጭሩ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

ፍትሕን ማስፈን ከሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች አንዱ ነው፡፡ ፍትሕ የሚለው ቃል የሚገልጸው በሕግ መሠረት ማስተዳደርን፣ መዳኘትን፣ ትክክለኛ ፍርድ መስጠትንና ማግኘትን ነው፡፡ ፍትሕን

[6] በዐማራ ክልል ሕገ መንግሥት የተደነገጉት የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ከተደነገጉት ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡

የማስፈን ሥራ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት የበላይነት እንደ ተጠበቀ ኾኖ፣ የዐማራን ክልል ሕገ መንግሥት የበላይነት በማክበር የሚከናወን ነው፡፡ ይኽም በዐማራ ክልል ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9 (1) "ይህ ሕገ-መንግስት የብሔራዊ ክልሉ የበላይ ሕግ ነው፡፡ ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሠራር፣ እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሣኔ ከዚህ ሕገ-መንግሥት ጋር የሚቃረን ሆኖ ሲገኝ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡" በማለት ተደንግጓል፡፡ ይኽም በክልሉ ፍትሕን የማስፈን ሥራ የክልሉን ሕገ መንግሥት የበላይነት በማክበርና በማስከበር ላይ የተመሠረተ ነው ማለት ነው፡፡ የሕገ መንሥቱን የበላይነት የሚቃረን ዐዋጅ፣ መመሪያና ደንብ ተፈጻሚ አይኾንም፡፡ የአስተዳደር ሥራም፣ ፍርድ የመስጠት ተግባርም መከናወን ያለበት የሕገ መንግሥቱን የበላይነት በመጠበቅ ነው ማለት ነው፡፡

ማንኛውም ሰው ፍትሕ የማግኘት መብት እንዳለው በአንቀጽ 37 (1) "ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው፡፡" በማለት ተደንግጓል፡፡ የወንጀልና የፍትሐ ብሔር ጉዳዮችን ለፍርድ ቤት በማቅረብ ፍርድ ማግኘት ወይም አስተዳደራዊ ጉዳየዮችን ለሚመለከተው ሕጋዊ አካል በማቅረብ ፍትሕ ማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብት ነው፡፡ ሕግ ተጥሷል ወይም ዲሞክራሲያዊ መብት አልተጠበቀም የሚል ሰው ለመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው ሰው በማቅረብ ፍትሕ ማግኘት ከሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች አንዱ ነው፡፡

የክልሉን ሕዝብ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ማስከበር የክልሉ ሕገ መንግሥት ዓላማዎች ናቸው፡፡ ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ፣ የማይጣሱና የማይገፈፉ መኾናቸውም በአንቀጽ 10 (1) ተደንግጓል፡፡ የአሰብአዊ መብቶችም በዐማራ ክልል ሕገ መንግሥት ከአንቀጽ 14 እስከ አንቀጽ 28 ተደንግገዋል፡፡ እነዚኽና ሌሎችም የሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች ተዘርዝረው በክልሉ ሕገ መንግሥት ከአንቀጽ 14 እስከ አንቀጽ 28 ተደንግገዋል፡፡ ዓላማዎቹም በሕይወት የመኖር መብት፣ የአካል ደህንነት መብት፣ የነፃነት መብት፣ በኢሰብአዊነት ያለመያዝ መብት፣ የተያዘ ሰው መብቶች፣ የተከሰሰ ሰው መብት፣ በጥበቃ ሥር ያለና በፍርድ የታሰረ ሰው መብቶች፣ በወንጀል ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ ያለመከሰስ መብት፣ በአንድ ወንጀል ድጋሚ ያለመቀጣት መብት፣ የክብርና የመልካም ስም መብት፣ የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት፣ የሃይማኖት፣ የኅሊናና የእምነት ነፃነት የሚሉ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በአንቀጽ 28 "ኢትዮጵያ ባፀደቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና በሌሎች የአገሪቱ ሕጎች ውስጥ "በሰው ልጆች ላይ የተፈፀሙ ወንጀሎች" ተብለው የተወሰኑትን በተለይም የሰው ዘር ማጥፋትን፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ መውሰድን፣ በአስገዳጅ ሁኔታ ሰውን መሰወርን ወይም ኢሰብአዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈጸሙ ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ የማይታገድ፣ በሕግ አውጭው ክፍልም ሆነ በማንኛውም የመንግሥት አካል ውሳኔ በምህረት ወይም በይቅርታ የማይታለፍ" መኾኑ ተዘርዝረው ተደንግገዋል፡፡

በዐማራ ክልል ሕገ መንግሥት አንቀጽ 25፣ ኹሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ስለ መኾናቸው የተደነገገው ከሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች አንዱ ነው፡፡ በዚኽ አንቀጽ ድንጋጌም፣ "ሁሉም ሰዎች

በሕግ ፊት እኩል ናቸው፡፡ በመካከላቸው ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር-ብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ፣ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግባቸው ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው፡፡" የሚል ነው፡፡

በክልሉ ሕገ መንግሥት ከአንቀጽ 29 እስከ አንቀጽ 44 የሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች ዲሞክራሲያዊ መብቶች በሚል የተደነገጉት ናቸው፡፡ በተጠቀሱት አንቀጾች የተደነገጉት ዲሞክራሲያዊ መብቶች አመለካከትንና ሐሳብን በነፃ የመያዝና የመግለጽ መብት፣ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት፣ የመደራጀት መብት፣ የመዘዋወር ነፃነትና የመኖሪያ ቦታ የመመሥረት መብት፣ በሕዝባዊና መንግሥታዊ ሥራዎች የመሰማራት መብት፣ የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶች፣ የሴቶች መብት፣ የሕፃናት መብት፣ ፍትሕ የማግኘት መብት፣ የመምረጥና የመመረጥ መብት፣ የንብረት መብት፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል መብቶች፣ የሠራተኞች መብቶች፣ የልማት መብት፣ የአካባቢ ደህንነት መብት ማስከበር የሚሉት ናቸው፡፡

ከሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች መካከል የብሔር-ብሔረሰቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ማክበር የሚለው ይጠቀሳል፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 (1) "ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ያለው መብቱ በማናቸውም መልኩ ያለ ገደብ የተጠበቀ ነው፡፡" በማለት የተደነገገው በዐማራ ክልል ሕገ መንግሥትም በአንቀጽ 39 የተጠበቀ መኾኑ ተደንግጓል፡፡ በዚኹ መሠረት በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 1፣2፣3 እና 6 የዐማራ፣ የኽምራ፣ የአዊና የኦሮሞ ብሔር-ብሔረሰቦች የየራሳቸውን ማንነት የመጠበቅና የማክበር፣ ቅርሳቸውንና ታሪካቸውን የመንከባከብና የማበልጸግ እንዲኹም በቋንቋቸው የመጠቀም፣ ቋንቋቸውን የማሳደግ፣ ባህላቸውን የመግለጽ፣ የማክበርና የማስፋፋት መብት ያላቸው መኾኑ ተደንግጓል፡፡

በክልል የሚኖሩ ብሔር-ብሔረሰቦች በየራሳቸው መልክዓ-ምድራዊ ክልል ውስጥ የየራሳቸውን ጉዳይ በየራሳቸው የመጨረስና ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር እንዲኹም በፌዴራሉ መንግሥት ውስጥ በነፃነት፣ ተገቢና ፍትሐዊ በኾነ ውክልና ተሳትፎ የማድረግ መብታቸው ተረጋግጧል፡፡ መብቶቻቸውም በየሰፈሩበት መልክዓ-ምድር እያንዳንዳቸው ራሳቸውን የሚያስተዳድሩባቸውን መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋምና በፌዴራሉ መንግሥት አስተዳደር ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና ማግኘትን ያጠቃልላል፡፡ የተጠቀሱት መብቶች በዐዋጅ ቁጥር 130/1998 ለአርጎባ ብሔረሰብ፣ በቅርቡ ደግሞ በዐዋጅ ቁጥር 255/2010 ለቅማንት[7] ብሔረሰብ ተፈቅደዋል።

[7]በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 (5) እና በዐማራ ብሔራዊ ክልላዊ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 (7) "ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ" ማለት ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ሕልውና አለን ብለው የሚያምኑ፣ የሥነ-ልቦና አንድነት ያላቸው፣ በአብዛኛው በተያያዘ መልክዓ-ምድር የሚኖሩ ናቸው የሚለውን ድንጋጌ የቅማንት ሕዝብ አያሟላም በማለት የዐማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት መጀመሪያ ላይ ጥያቄውን ውድቅ

የዐማራ ክልል መንግሥት በክልሉ የሚኖሩ የዐማራ፣ የኽምራ፣ የአዊና የኦሮሞ ብሔር-ብሔረሰቦችና ሌሎች ሕዝቦች የየራሳቸውን ማንነት የመጠበቅና የማክበር፣ ቅርሳቸውንና ታሪካቸውን የመንከባከብና የማበልጸግ እንዲሁም በቋንቋቸው የመጠቀም፣ ቋንቋቸውን የማሳደግ፣ ባህላቸውን የመግለጽ፣ የማክበርና የማስፋፋት መብት ተከብሮላቸዋል፡፡ በሰፈሩበት ምልክዓ-ምድር በኹሉም ደረጃዎች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር፣ የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው የመወሰን መብታቸው መከበሩን፣ እንዲኹም ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩባቸውን መንግሥታዊ ተቋማት ማቋቋማቸውን፣ በክልሉም፣ በፌዴራል መንግሥቱም ሚዛናዊ ውክልና ማግኘታቸውን፣ የክልሉ መንግሥት ያምናል፡፡ ከዚኽ በላይ በተመለከትነው ንዑስ ርእስ ሥር የተገለጹት የሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች በክልሉ በሚገኙ የብሔረሰብ አስተዳደሮች እየተተገበሩ ናቸው፡፡ የብሔረሰብ አስተዳደሮቹ መንግሥታዊ ተቋማትን አቋቁመው ራሳቸውን በራሳቸው ያስተዳድራሉ፤ ባህሎቻቸውን ያበለጽጋሉ፣ ያዳብራሉ፣ ያስፋፋሉ እንዲኹም ይንከባከባሉ፣ በቋንቋዎቻቸው ይማራሉ፡፡ በኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር በኦሮምኛ ቋንቋ ይዳኛሉ፡፡

በብሔረሰብ አስተዳደሮች መደበኛ ትምህርት በአፍ መፍቻ ቋንቋ የሚሰጥባቸው ትምህርት ቤቶች በርካታ ናቸው፡፡ በዚኹ መሠረትም በአዊ ብሔረሰብ አስተዳደር ለኹለት መቶ ሠላሣ ሰባት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አዊኛ ቋንቋ የማስተማሪያ ቋንቋ ኾኖ ያገለግላል፡፡ አንደዚኹም ለዐምስት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በሙከራ ደረጃ አዊኛ ቋንቋ በትምህርት ዓይነትነት ይሰጣል፡፡[8] በዋግ ኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር የአንድ መቶ ዐሥራ አንድ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በኻምጣኛ ቋንቋ ይማራሉ፡፡ ቁጥራቸው በማነሱ ምክንያት ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር ላልቻሉ በአበርገሌ ለሚኖሩ ትግርኛ ተናጋሪዎች በአራት ትምህርት ቤቶች በራሳቸው በትግርኛ ቋንቋ ይማራሉ፡፡[9] በተጨማሪም ዜሮ ክፍል የሚባሉ በትግርኛ ቋንቋ ፊደል

አድርጎት ነበር (በዚኽ ድንጋጌ አንድን ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ ማንነት ለመግለጽ ቅርስና ታሪክ የሚሉት በመመዘኛነት አልተካተቱም፡፡)፡፡ ይኹን እንጂ ጥያቄውን ያቀረበው ኮሚቴው አቤቱታውን ለፌዴሬሽን ምክር ቤት አቀረበ፡፡ የፌዴሬሽን ምክር ቤትም አቤቱታውን መርምሮ የክልሉ መንግሥት ጥያቄውን እንደገና እንዲመረምር አደረገ፡፡ በዚኹ መሠረትም የዐማራ ክልል ምክር ቤት "ሕገ መንግሥቱን ጭምር ወደ ጎን በመግፋት፣ የሕዝቡን የማንነትና ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ ለማስተናገድ" ወሰነ፡፡ "በዚህም መሠረት ከ2010 ዓ. ም. ጀምሮ የቅማንት አስተዳደር 69 ቀበሌዎችን በያዙ ሁለት ወረዳዎች የተዋቀረ ልዩ ዞን ሆኖ እንዲደራጅና አዲሱ አስተዳደርም በዚሁ አግባብ ወደ ሥራ እንዲገባ የክልሉ ም/ቤት ወስኗል፡፡" (ቹቹ፣ 2011፤ 226)፡፡ በውሳኔው ቅር የተሰኘው ለቅማንት ሕዝብ የራስ አስተዳደር ጥያቄ ያቀረበው ኮሚቴ በቅማንት አስተዳደር ሥር መካተት የሚገባቸው ቀበሌዎች በዐማራ አስተዳደር ሥር የሚገኙ ቀበሌዎች እንዳሉ ቅሬታውን በማቅረቡ በዐሥሩ ቀበሌዎች የሚኖረው ሕዝብ ድምፅ እንዲሰጥ ተደርጎ የስምንቱ ቀበሌዎች በቀደመው የዐማራ ወረዳ ሥር መተዳደር እንደሚፈልጉ መርጠዋል፡፡ "የዐማራ ክልል ምክር ቤት የሕዝበ ውሳኔ ድምፅ ሳይሰጥ ለ69 ቀበሌዎች የራስ አስተዳደር መብት መስጠቱ ተገቢ አይደለም" በማለት የሚተቹም አሉ፡፡ "ቅማንት ከጎንደር ዐማራ የተለየ ስለአልኾነ የራስ አስተዳደር የሚባለው ጥያቄ ትክክል አይደለም" በማለት የሚቃወሙ የቅማንት ተወላጆች አሉ፡፡

[8]አቶ የሺዋስ ይስማው፣ ዕድሜ 59፣ የትምህርት ደረጃ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ በአዊ ብሔረሰብ አስተዳደር የአዊኛ ቋንቋ ዕድገት ምርምርና ሥልጠና ባለሙያ፤ መጋቢት 18 ቀን 2011 ዓ. ም. የሰጡት ቃለ መጠይቅ፡፡

[9]አቶ አብጨ በየነ፣ ዕድሜ 41፣ የመጀመሪያ ዲግሪ፣ በዋግ ኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ትምህርት መምሪያ የኻምጣኛቋንቋ ልማት ቡድን መሪ መጋቢት 18 ቀን 2011 ዓ. ም. የሰጡት ቃለ መጠይቅ፡፡ በተጨማሪም መምህር አእመረ ፀሐዩ ንጋቱ የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ የግእዝ ቋንቋ መምህር ታኅሣሥ 17 ቀን 2012 ዓ. ም. በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሰጡት ቃለ መጠይቅ እንዳስረዱት የትምህርት ቤቶቹ ብዛት 6 ሲኾን ስማቸውም ገነት፣ አድዘልኝ፣ አርሲግ፣ ባኽለ፣ ቡልደ እና በበ ናቸው፡፡ የኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ለእነዚኽ

የሚቆጥሩባቸውና ንባብ የሚማሩባቸው ወደ መደበኛ ትምህርት መሸጋገሪያ በትግርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚሰጥባቸው አሉ፡፡[10] እንደዚኹም፣ በኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ኹለት መቶ አንድ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአፋን ኦሮሞ ይማራሉ፡፡ በዐሥራ ኹለት የኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ አፋን ኦሮሞ በትምህርት ዐይነትነት ይሰጣል፡፡[11] ይኽም በመኾኑ በእነዚኽ የብሔረሰብ አስተዳደሮች ውስጥ ከሚገኙት የዐማራ ሕፃናት መካከል አብዛኞዎቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዳይማሩ ተደርገዋል፡፡ ከዛም አልፎ በኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ውስጥ የሚገኙ ዐማራዎች በኦሮምኛ ቋንቋ እንዲዳኙና እንዲተዳደሩ በመደረጉ በክልላቸው ውስጥ እየኖሩ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የመጠቀም መብታቸው ያልተከበረ መኾኑንም እንመለከታለን፡፡

በዐማራ ክልል የመገናኛ ብዙኀን በኽምጣኛ፣ በአዊኛና በኦሮምኛ ቋንቋዎች የሬዲዮና የቴሌቪዥን መርሐ ግብሮችን ያቀርባሉ፡፡ በክልሉ በሚደረጉ ክልል አቀፍ ዝግጅቶች በተጠቀሱት ቋንቋዎች የቀጥታ ዘገባዎችን ያቀርባሉ፡፡ የዐማራ ክልል ምክር ቤት በ1997 ዓ. ም. በወሰነው መሠረት በኻምጣኛ፣ አዊኛ እና ኦሮምኛ ቋንቋዎች በሬዲዮ መርሐ ግብሮችን ማቅረብ ተጀመረ፡፡ ለእያንዳንዱ ቋንቋ የተፈቀደው የአየር ጊዜ 15 ደቂቃ ብቻ ነበር፡፡ የሚያቀርቡበት ሰዓትም አዊኛ ሰኞ ከምሽቱ 12፡15 እስከ 12፡30፣ ኻምጣኛ ረቡዕ ከምሽት 12፡15 እስከ 12፡30 እና ኦሮምኛ ዐርብ ከምሽቱ 12፡15 እስከ 12፡30 ነበር፡፡ ይኹን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲኽ የሬዲዮ ጣቢያው ሰፋ ያለ የአየር ጊዜ ሥራ ላይ በመዋሉ ምክንያት በአኹኑ ጊዜ ለእያንዳንዳቸው የተፈቀደው የአየር ጊዜ በሳምንት ወደ አራት ሰዓት ከፍ ብሏል፡፡ በቋንቋው ለየብሔረሰባቸው በሚያቀርቧቸው ዝግጅቶች ለመዝናኛዎች (በአብዛኛው በየቋንቋቸው ለተዜሙ ዘፈኖች)፣ ለልዩ ልዩ ባህላዊና ታሪካዊ ክንዋኔዎች ትኩረት ይሰጣሉ፡፡ የእነዚኽ ብሔረሰቦች የሬዲዮ ፕሮግራም አዘጋጆች በዜና ማቅረቢያ መርሐ ግብራቸው በዞን አስተዳደሩ፣ በዐማራ ክልል፣ በኢትዮጵያና በዓለም የተከናወኑ ድርጊቶችን ይዘግባሉ፡፡ ቋንቋቸውን ለማበልጸግ የሚረዱ ዝግጅቶችንም ያቀርባሉ፡፡[12] ከሬዲዮ አገልግሎት በተጨማሪ ከላይ በተጠቀሱት የብሔረሰቦች ቋንቋዎች በዐማራ ክልል በኻምጣኛ፣ አዊኛ እና ኦሮምኛ ቋንቋዎች የቴሌቪዥን አገልግሎት መስጠት የተጀመረው በ2008 ዓ. ም. ሲኾን ለእያንዳንዳቸው የተመደበው የአየር ጊዜ በሳምንት ሦስት ሰዓት ነው፡፡[13]

---

ትምህርት ቤቶች የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪ መምህራን የቀጠረው በትግራይ ክልል በሚገኘው ማይጨው ከተማ ማስታወቂያ በማውጣት ነው፡፡ የማስተማሪያ መጻሕፍቱንም የገዛው ከትግራይ ክልል ነው ብለዋል፡፡

[10] በተለምዶ ሳተላይት የሚባሉት ት/ቤቶች ብዛት አራት ሲኾኑ ስማቸውም ጠጥአርቀ፣ ጁ፣ ጀምጀም እና ሸውርት ናቸው፡፡ ነገር ግን፣ ወደትግራይ በተከለሉ አገውኛ ተናጋሪዎች የሚኖሩባቸው በርካታ ቀበሌዎች በኮረምና አበርገሌ ወረዳዎች አዋሳኝ ቢኖሩም በራሳቸው ቋንቋ ለመማር በተደጋጋሚ ጠይቀው አልተፈቀደላቸውም (መምህር አእመረ ፀሐዩ ንጋቱ የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ የግእዝ ቋንቋ መምህር ታኅሣሥ 17 ቀን 2012 ዓ. ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሰጡት ቃለ መጠይቅ)፡፡

[11] ወ/ሮ አሰገድ ሚሪሳ፣ የትምህርት ደረጃ ኹለተኛ ዲግሪ፣ በዐማራ ክልል የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር የትምህርት መምሪያ ኃላፊ፣ መጋቢት 19 ቀን 2011 ዓ. ም. የሰጡት ቃለ መጠይቅ፡፡

[12] አቶ አንተነህ መንግሥቴ ፀጋ፣ የዐማራ ብዙኀን መገናኛ ድርጅት ምክትል ሥራ አስኪያጅ፣ መስከረም 5 ቀን 2013 ዓ. ም. ከቀኑ 10፡30 ሰዓት፣ በጽሕፈት ቤታቸው የሰጡት ቃለ መጠይቅ፡፡

[13] አቶ አንተነህ መንግሥቴ ፀጋ፣ የዐማራ ብዙኀን መገናኛ ድርጅት ምክትል ሥራ አስኪያጅ፣ መስከረም 5 ቀን 2013 ዓ. ም. ከቀኑ 10፡30 ሰዓት፣ በጽሕፈት ቤታቸው የሰጡት ቃለ መጠይቅ፡፡

እንዲኹም በክልሉ የኅትመት መገናኛ ዘዴ አማካይነት በዐማራ ክልል በኻምጣኛ፣ አዊኛ እና ኦሮምኛ ቋንቋዎች በእያንዳንዳቸው በየዐሥራ ዐምስት ቀን አንድ ጊዜ በወር ደግሞ ኹለት ጊዜ ስምንት ገጽ ያላቸው ጋዜጦች እየታተሙ ለተጠቃሚዎች ይሰራጫሉ፡፡ በሦስቱም ቋንቋዎች ጋዜጣ መታተም የተጀመረው በ2003 ዓ. ም. ሲኾን በየጋዜጦቹ "ገጽታ" በሚል አምድ የየቋንቋዎቹ ተናጋሪዎች ባህል፣ ወግ፣ ታሪክ ይቀርባሉ፡፡ "ልማት" በሚል አምድ ደግሞ በብሔረሰብ አስተዳደሮቹና በክልሉ ውስጥ የተከናወኑ ዐበይት የልማት ሥራዎች ይዘገባሉ፡፡ እንደዚሁም "ማኅበራዊ" በሚል አምድ ሥርም የጤና፣ የትምህርት፣ የወጣቶችና የሴቶች ጉዳዮች በዝርዝር ይቀርባሉ፡፡ በዜና አምድም የዞኑ፣ የክልሉ፣ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ዜናዎች ይዘገባሉ፡፡[14]

በብሔረሰብ አስተዳደር ቋንቋዎች የሬዲዮ፣ የቴሌቪዥንና የጋዜጣ ኅትመት አገልግሎት ከመሰጠቱ በተጨማሪ የዐማራ ብዙኀን መገናኛ ድርጅት በሚያስተዳድራቸው የፌስቡክ እና የዩቲዩብ በአማርኛ፣ ኻምጣኛ፣ አዊኛና ኦሮምኛ ቋንቋዎች ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮጭ ይቀርባሉ፡፡ የሕገ መንግሥቱን መሠረታዊ መርኆዎች ለመተግበር ከተደነገጉት ዓላማዎች መካከል ማኅበራዊ ነክ ዓላማዎች ይጠቀሳሉ፡፡ በአንቀጽ ııı ንዑስ አንቀጽ ı ኹሉም የክልሉ ኑዋሪዎች የትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣ የንፁህ የመጠጥ ውኃ፣ የመጠለያ፣ የምግብና የማኅበራዊ ዋስትና እንዲኖራቸው ጥረት እንደሚደረግ ተደንግጓል፡፡ በዚኽ ደንጋጌ ከተዘረዘሩት ዓላማዎች መካከል በክልሉ በብሔር- ብሔረሰቦች ቋንቋዎች ትምህርት መሰጠቱ የብሔር-ብሔረሰቦችን መብት ማክበር ነው፡፡ የተጠቀሱትን ሕገ መንግሥቱ ዓላማዎች ቀጥለው በተጠቀሱት የክልሉ መዝሙር ሥንኞች መንፀባረቃቸውን እናስረዳለን፡፡

(1) የታታሪ ሕዝቦች - የታሪክ ማኅደር፣
(2) የአኩሪ ባህል አምባ - የድንግል አፈር፡፡
(3) የሕዝቦችሽ ተስፋ - ለሚ ክልላችን፣
(4) በሰላም በፍትሕ - በልማት ጉዟችን፣
(5) ተባብረን በሥራ - እንንከባኻለን፡፡

ከዚኽ በላይ ከተጠቀሱት ሥንኞች የመጀመሪያዎቹ ኹለት ሥንኞች ክልሉ ያሉትን ሀብቶች ይዘረዝራሉ፡፡ በሀብትነት የተቆጠሩትም፣ የክልሉ ታታሪ ሕዝቦች (ዐማራ፣ ኽምራ፣ አዊ፣ ኦሮሞና ሌሎችም የክልሉ ሕዝቦች)፣ የክልሉ ታሪክ፣ ባህልና ድንግል መሬት ናቸው፡፡ ታታሪ የሚለው ቅጽል የክልሉ ሕዝቦች ለሥራ ትጋት፣ ጥረትና ታታሪነት አላቸው ማለትን ይገልጻል፡፡ የሕዝቦቹ ታታሪነትና የሥራ ትጋት፣ ዕድገትንና ለውጥን ለማምጣት ያግዛል፡፡ ይኸም ለውጥ፣ ዕድገት ለማምጣት ተግቶ መሥራት አስፈላጊ መኾኑን ያሳውቃል፤ ይቀሰቅሳል፤ የሥራ ባህል እንዲዳብር ለማድረግ ያነሣሣል፡፡ በራስ የመተማመን ባህልንም እንዲጎለብት ያስተምራል ማለትን ይገልጻል፡፡ በ"የሕዝቦችሽ ተስፋ - ለሚ ክልላችን" በሚለው ሥንኝ ሕዝቦች በሚል ብዙ ቁጥር የተጠሩት

[14] አቶ አንተነህ መንግሥቱ ፀጋ፣ የዐማራ ብዙኀን መገናኛ ድርጅት ምክትል ሥራ አስኪያጅ፣ መስከረም 5 ቀን 2013 ዓ. ም. ከቀኑ 10:30 ሰዓት፣ በጽሕፈት ቤታቸው የሰጡት ቃለ መጠይቅ፡፡

በክልሉ ሕገ መንግሥት ድንጋጌዎች መረዳት እንደሚቻለው በአንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጾች አማራ፣ ኽምራ፣ አዊና ኦሮሞ ተብለው በስም የተጠሩትና በአንቀጽ 45 (3) በክልሉ የሚገኙ ነገር ግን በስም ያልተጠሩ "ብሔር-ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች" እና ሌሎችም በክልሉ መንግሥት የሚተዳደሩ ጠቅላላ ሰዎች ናቸው፡፡

በክልሉ ሕገ መንግሥት በስም የተጠሩትና ያልተጠሩት ሕዝቦች የወደፊት የሕይወት ተስፋ የተመሠረተው በአነስታይ ፆታ በተጠራችው ክልላቸው የተፈጥሮ ሀብት ላይ ነው፡፡ መዝሙሩ እንደሚገልጸው ሕዝቦቹ ተስፋቸውን የሰነቁባትና አለኝታቸው ያደረጓት ክልላቸው መሬት በለምነቱ እንድም፣ ሲታረስ ጥሩ ምርት ይሰጣል፡፡ የመሬት ለምነት አለኝታቸው መኾኑን መዝሙሩ ይገልጻል፡፡ የሕዝቦች መመኪያ የተደረገው የክልላቸው ለምነት ከግብርና ሥራ ጋር የተገናኘ ነው፡፡ ግብርናም የእርሻና የከብት እርባታ ሥራ ነው፡፡ ለም መሬት ንብ ለማነብ፣ ዕጣንና ሙጫ ለማምረት ያስችላል፡፡ ክልሉ ለም መባሉ ዓመት እስከ ዓመት የሚፈሱ ወንዞች ያሉትና በደን የተሸፈነ መሬት ማለትም ይኾናል፡፡ ይኸም በመዝሙሩ የክልሉ ሕዝቦች አለኝታ፣ መመኪያ፣ መኩሪያ ተደርጎ የተገለጸው ተፈጥሮ መኾኑን ያስረዳል፡፡ መዝሙሩ ኹለተኛውና ሦስተኛው ሥንኞች ሕዝቦች የክልላቸውን ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ማለትም ኹከት፣ ረብሻ፣ ጦርነት የሌለበትና የተረጋጋ ክልል ለማድረግ፣ ሰዎች በሕግ መሠረት የሚዳኙበትንና ትክክለኛ ፍርድ የሚያገኙበትን ሥርዓት ለመፍጠር የመተባበር፣ የመረዳዳት፣ የመተጋገዝ እንቅስቃሴ እንደሚያደርጉ ይገልጻሉ፡፡ "በልማት ጉዟችን" በሚለው ሐረግ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገትንና ብልፅግናን ለማምጣት ሕዝቦች በአእምሯቸው የሚያሰላስሉትን፣ በጉልበታቸው የሚያደርጉትን እንቅስቃሴና የሚከውኑትን ተግባር በማስተባበር ለልማት እንደሚተጉ ይገልጻል፡፡ የክልሉ ሕዝቦች ተረዳድተው፣ ተባብረው፣ ተጋግዘው ክልላቸውን እንደሚያበለጽጉ፣ እንደሚያሳድጉ መዝሙሩ ይገልጻል፡፡ በመዝሙሩ የክልላቸውን ለም መኾን በሕፃናቱ አእምሮ ያሰርጻል፡፡ ሰላምንና ፍትሕን ለማስፈን፣ ልማትን ለማምጣት በኅብረት፣ በመረዳዳት፣ በአንድነት የመሥራትን አስፈላጊነት ያስተምራል፡፡

## 2. 2) የዐማራ ሕዝብ ከሌሎች ከኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ ለመኖር ያለውን እምነት ማንፀባረቅ

የዐማራ ክልል ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 4 መዝሙሩ "የክልሉ ህዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ ለመኖር ያለውን እምነት የሚያንፀባርቅ" እንዲኾን ይደነግጋል፡፡ መዝሙሩ የተጠቀሰውን ድንጋጌ ማንፀባረቅ፣ አለማንፀባረቁን ከመመርመራችን በፊት "የክልሉ ሕዝብ" እና "ሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች"የሚሉትን ሐረጎች በአጭሩ እንመለከታለን፡፡ "የክልሉ ሕዝብ" የሚለው በዐማራ ክልል ሕገ መንግሥት በስም የተጠሩትንና በስም ያልተጠሩትን የክልሉ መንግሥት የሥልጣን ባለቤቶችን ነው፡፡ በሕገ መንግሥቱ በስም የተጠሩት የአማራ፣ የኽምራ፣ የአዊና የአሮሞ ብሔር-ብሔረሰቦች ናቸው፡፡ በስም ያልተጠሩት ደግሞ በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 45 (3) "በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች" በማለት የተገለጹት ናቸው፡፡ "ሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች" የሚለው ሐረግ የሚገልጸው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47

(1) የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባል ክልሎች የሚገኙትን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ነው፡፡

ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚለው ጽንሰ ሐሳብ በሕዝብ ፈቃድ የተመሠረተ ፤ በተወሰነ ጊዜ ነፃና ትክክለኛ በሆነ የሕዝብ ፈቃድ ሁሉም ሕዝብ በእኩልነት ተሳታፊ የሚሆንበት ምርጫ የሚገለጽበት፣ የግለሰብ የምርጫ ድምፅ አሰጣጥ በምሥጢራዊ ሥርዓት የሚከናወንበት የመንግሥት ሥርዓት፣ ሰብአዊ መብቶችን የሚያከበር፣ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መንግሥት ከሚያራምደው አስተሳሰብ የተለየ የፖለቲካ አመለካከት መከተላቸውን የሚቀበል፣ ልዩ ልዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች የየራሳቸውን ባሕል የማሳደግ መብታቸውን የሚያረጋገጥ፣ ሥልጣኑ በሕግ የተገደበ፣ እንዲያስተዳድረው ለመረጠው ሕዝብ ተጠሪና ተጠያቂ መኾኑን ማረጋገጫ ሥርዓት የመሠረተ መንግሥት ማለትን ይገልጻል (የሕገ መንግሥት ኮሚሽን፣ 1986፤ 4-5)፡፡

"ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት" የሚለው በአጭሩ ሲገለጽ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች መብት፣ ነጻነት ጥቅምና ፍላጎት የተከበረበት፣ የሕግ የበላይነት የሠፈነበት ሥልጣን ሕዝብ በሚመረጡ ተወካዮቹ እጅ የሚኾንበት ሥርዓተ መንግሥት ነው ማለት ነው፡፡ የዐማራ ክልል ሕዝብ ከተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ጋራ አብሮ የመኖር እምነቱ እውን የሚኾነው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ከአንቀጽ 29 እስከ አንቀጽ 44 የተደነገጉት ዴሞክራሲያዊ መብቶች ይከበራሉ ብሎ ከማመን የሚመነጭ ነው፡፡ ዴሞክራሲያዊ መብቶቹ፣ የአመለካከትና ሐሳብን በነጻ የመያዝና የመግለጽ መብት፤ የመሰብሰብ መብት፤ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነጻነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት፤ የመደራጀት መብት፤ የዜግነት መብት፤ የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶች፤ የሴቶች መብት፤ የሕፃናት መብት፤ ፍትሕ የማግኘት መብት፤ የመምረጥና የመመረጥ፤ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች መብት፤ የንብረት መብት፤ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባህል መብቶች፤ የሠራተኞች መብት፤ የልማት መብት እና የአካባቢ ደህንነት መብት በማለት ተደንግገዋል፡፡ ከዴሞክራሲያዊ መብቶች በተጨማሪ የሰብአዊ መብቶች መከበር የዐማራ ሕዝብ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋራ አብሮ ለመኖር እምነት እንዲኖረው እንደሚያደርግ ከሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ የተጠቀሱት ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበሩት የኢትዮጵያን ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክን በመሠረቱት ክልሎችና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ነው፡፡

በድንጋጌው "እምነት" የሚለው ቃል በሕገ መንግሥቱ ባለው ዐውዳዊ ፍቺ እርግጠኛነት፣ ኃላፊነትና ታማኝነት ማለት ነው፡፡ እርግጠኛነት የሚለውም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በተቋቋመበት ሕገ መንግሥት አንቀጽ 10 (2) የተደነገገው የዜጎችና የሕዝቦች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበሩ መኾናቸው ተደንግጓል፡፡ ኀላፊነት የሚለው ቃል ተያዥነት፣ ዋቢነትና ተጠያቂነት የሚል ፍቺ አለው፡፡ ይኽም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 13 (1) በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል መንግሥትና የክልል ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚ እና የዳኝነት አካሎች በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉትን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የማክበርና የማስከበር ኀላፊነትና ግዴታ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ እነዚኽን መብቶች የሚጻረሩ ሕጎች በክልሎች ሕግጋተ

መንግሥታት ቢደነገግ ወይም የተጠቀሱትን መብቶች የሚጻረር ውሳኔ በማንኛውም አካል ቢተላለፍ ተፈጻሚ አይኾንም፡፡ ይኸም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9 (1 እና 2) የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የሀገሪቱ የበላይ ሕግ በመኾኑ ከዚኽ ሕገ መንግሥት ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሠራር፣ እንዲኹም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡ ማንኛውም ዜጋ፣ የመንግሥት አካል፣ የፖለቲካ ድርጅት፣ ማኅበር እንዲኹም ባለሥልጣን በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት የተደነገገውን የማክበርና ለሕገ መንግሥቱ ተገዥ የመኾን ኃላፊነት አለበት፡፡ በአንቀጽ 51 (1) እንደተደነገገው የኢትዮጵያን ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥትን የመጠበቅና የመከላከል ሥልጣንና ተግባር የኢፌዴሪ መንግሥት ነው፡፡

በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ የመኖር እምነት ምን ማለት እንደኾነ ከዚኽ በላይ ተገልጿል፡፡ ቀጥለን የዐማራ ክልል ሕዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ጋር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ ለመኖር ያለውን እምነት በክልሉ መዝሙር መንጸባረቁን ከሚከተሉት ሥንኞች መረዳት እንችላለን።

(6) የአማራነትን ክብር - ደማቅ አርማ ይዘን፣
(7) ከሌሎች ሕዝቦች ጋር - እኩል ተከባብረን፣
(8) በፍቅር በአንድነት - አብረን እንዘልቃለን፡፡

"የአማራነትን ክብር - ደማቅ አርማ ይዘን፣" በሚለው ሥንኝ መልእክት "እኛ" በሚል አንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር አመልካች ተውላጠ ስም የተነገረ ነው፡፡ ተውላጠ ስሙም በክልሉ የሚኖሩ በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 (5) "ብሔር-ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች" በማለት የተጠሩትንና በአንቀጽ 39 (6) በብሔረሰባቸው ስም የተጠሩትን "የኸምራ፣ የአዊና የኦሮሞ ሕዝቦች"ን ኹሉንም ይጠራል፡፡ በዐማራ ክልል የሚኖሩ በስም የተጠሩትና በወል ስም ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ በማለት የተጠሩት የዐማራን ክብርና አርማ በመያዝ "ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች" [ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች] ጋር በፍቅር ላይ የተመሠረተ ትብብርና አንድነት እንደሚፈጥሩ መዝሙሩ ይቀሰቅሳል፡፡ በዐማራ ክልል የሚገኙ ብሔር-ብሔረሰቦች በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ረፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 (1-5) በተደነገጉትና በዐማራ ክልል ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 39 (1-6) በተደነገጉት መብቶች መሠረት የየራሳቸውን የብሔረሰብ አስተዳደሮችና ወረዳዎች አቋቁመው ራሳቸውን በራሳቸው ያስተዳድራሉ፡፡ በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 8 (1-2) የዐማራ ክልል ብሔር-ብሔረሰቦች የክልሉ የበላይ ሥልጣን ባለቤቶች መኾናቸው ተደንግጓል፡፡ የበላይነታቸው የሚገለጸውም በሚመርጧቸው ተወካዮችና ራሳቸው በቀጥታ በሚያደርጉት ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ አማካኝነት ነው፡፡ ይኹን እንጂ መዝሙሩ የክልሉ ብሔረሰቦች ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ጋር በፍቅር ተባብረውና አንድነትን ጠብቀው የዐማራውን ክብር (ዐማራው የሚታወቅበትንና የሚለይበትን ገናናነትንና ታዋቂነትን) ይዘው አብረው እንዲኖሩ ይቀሰቅሳል፡፡ በዐማራ ክልል የሚኖሩ ብሔር-ብሔረሰቦች በሌሎች ክልሎች ከሚኖሩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ጋር ትብብርና አንድነት

የሚመሠርቱት የዐማራነትን ክብር መለያቸው፣ መታወቂያቸው፣ ደማቅ ዐርማቸው አድርገው እንዲኾን በመዝሙሩ ማስተማር፣ ማንቃት ዐማራ ያልኾኑትን ብሔረሰቦች ማንነት የዘነጋ ነው፡፡

ይኽ በመዝሙሩ የቀረበው ሐሳብ እንደ ዐማራው ኹሉ ሌሎች የክልሉ ብሔረሰቦች የራሳቸውን ልዕልና፣ ገናናነት፣ ታዋቂነት እንደያዙ ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ጋር በፍቅር ተባባረው በአንድነት እንደኖሩ አለማስተማር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥትና በዐማራ ክልል ሕገ መንግሥት ለብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የተደነገገውን መብት መቃረን ነው፡፡ በክልሉ መዝሙር የመጀመሪያው ሥንኝ የመጀመሪያ ሐረግ “የታታሪ ሕዝቦች”፣ በሦስተኛው ሥንኝ የመጀመሪያ ሐረግ ደግሞ “የሕዝቦችሽ ተስፋ” በማለትና መዝሙሩን በጠቅላላ በብዙ ቁጥር በማቅረብ በክልሉ ብሔር-ብሔረሰቦች እንደሚኖሩ ዕውቅና ይሰጣል፡፡ ይኹን እንጂ በስድስተኛው ሥንኝ “የአማራነትን ክብር - ደማቅ አርማ ይዘን” በማለት ዕውቅና ይነሣል፡፡ ስለኾነም መዝሙሩ በኢፌዲሪና በዐማራ ክልል ሕግጋተ መንግሥታት በዐማራ ክልል ለሚኖሩ ብሔረሰቦች የተሰጠውን መብት የሚቃረን ሐሳብ በመዝሙሩ ተንጸባርቋል፡፡ “የአማራነትን ክብር - ደማቅ አርማ ይዘን” በሚለው ሥንኝ የተገለጸው ሐሳብ ለብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ከተሰጠው ሕገ መንግሥታዊ መብት የሚቃረን ከመኾኑም በላይ በክልሉ መዝሙር፦

(1) የታታሪ <u>ሕዝቦች</u> - የታሪክ ማኅድር፣
(3) የ<u>ሕዝቦች</u>ሽ ተስፋ - ለሚ ክልላችን፣ (አጽንኦት የተጨመረ)

በማለት በብዙ ቁጥር የጠራቸውን በክልሉ የሚኖሩ ብሔረሰቦች ታሳቢ ያደረገ አይደለም፡፡

በክልሉ መዝሙር የመጀመሪያው ሥንኝ የመጀመሪያ ሐረግና በሦስተኛው ሥንኝ የመጀመሪያ ሐረግ “ሕዝቦች” የሚለው ብዙ ቁጥር ገላጭ ቃል የሚጠራው በክልሉ የሚገኙትን ብሔር-ብሔረሰቦች ነው፡፡ በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 (6) እና አንቀጽ 45 (2) በክልሉ ውስጥ ለሚገኙት “የኽምራ፣ የአዊና የኦሮሞ ሕዝቦች” ራስን በራስ ማስተዳደር እስከ መገንጠል ድረስ መብታቸው መከበሩና የየራሳቸው ምክር ቤት እንደሚኖራቸው ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም በአንቀጽ 45 (3) በክልሉ ውስጥ ለሚገኙ ሌሎች “ብሔር- ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ” በክልሉ የሚኖራቸው ውክልና በልዩ ኹኔታ እንደሚታይ ተረጋግጧል፡፡ በዚኹ መሠረትም የአርጎባና የቅማንት ብሔረሰቦች የየራሳቸውን የወረዳ አስተዳደሮች መሥርተዋል፡፡ በዐማራ ሕገ መንግሥት በክልሉ ውስጥ የሚኖሩ ብሔር-ብሔረሰቦች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብታቸው በመረጋገጡ ሦስት የብሔረሰብ አስተዳደሮችና ኹለት የወረዳ አስተዳደሮች ተቋቁመዋል፡፡ በዐማራ፣ በኽምራ፣ በአዊና በኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደሮችና በአርጎባና በቅማንት ወረዳዎች የሚኖሩት ብሔረሰቦች በክልሉ ከዐማራው ብሔር እኩል መብት ያላቸው መኾኑ ከተረጋገጠ በተለያዩ ክልሎች ከሚኖሩት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጋር በሚደረገው ግንኙነት ማንነታቸው መከበሩ ተረጋግጦ መኾን ይገባዋል፡፡[15]

[15]የዐማራ ክልል ተብሎ መጠራቱ በክልሉ የሚኖሩትን የኽምራ፣ የአዊ፣ የኦሮሞ፣ የአርጎባ፣ የቅማንትና የሌሎችም ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በክልሉ እኩል መብት እንደአላቸው አይነግርም፡፡

የዐማራውን ክብር ብቻ ከፍ ማድረጉ በክልሉ የሚኖሩትን የተለያዩ ብሔረሰቦች ተወላጆችን ያስከፋል፤ አስከፍቷልም፡፡ "የአዊ ልጅ ራሱን ሳይጨምር እንዴት ስለዐማራ ክብር ይዘምራል? የሚል ጥያቄ በማንሳት ውስጥ ውስጡን ቢብላላም ቅሬታውን በድፍረት ለማቅረብ ግን ይፈራል፡ ፡ ስለኾነም በዚኽ የብሔረሰብ አስተዳደር ጉዳዩ አይነኬ ኾኖ ቆይቷል፡፡"[16] በኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደርም ውስጥ ውስጡን የሚብላል ተመሳሳይ ተቃውሞ አለ፡፡ "እኛን አግልሎ 'ከሌሎች' ጋራ የሚለው እነማንን ነው?" የሚል ጥያቄ የሚያነሡ የኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ነዋሪዎች አሉ፡፡[17] ከኹሉም የብሔረሰብ አስተዳደሮች ጠንከር ያለ ተቃውሞ ያለው የከምሴ ኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ትምህርት በኣፋን ኦሮሞ በሚሰጥባቸው ኹለት መቶ አንድ የአንደኛ ደረጃ እና ዐሥራ ኹለት የኹለተኛ ደረጃ ምህርት ቤቶች የዐማራ ክልል መዝሙር አይዘመርም፡፡ ምክንያቱ "ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋራ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አብረን የምንኖረው የራሳችንን ማንነት ይዘን እንጂ የዐማራነትን ክብር ይዘን አይኾንም፡፡ "የአማራነትን ክብር - ደማቅ አርማ ይዘን" "የሚለው ሥንኝ ያለበትን መዝሙር ተማሪዎቻችን እንዲዘምሩ ማድረግ ኦሮሞነትን ትተው ዐማራነትን እንዲቀበሉ ማስተማር ነው የሚል ተቃውሞ በብሔረሰብ አስተዳደሩ በመኖሩ ነው፡፡"[18] በመዝሙሩ የዐማራ ክብርና ዐርማ መጠቀሱ ቅሬታ ያላቸው ወገኖች "እኛነታችን" በመተው ዐማራነትን ተቀበሉ የሚለው አገላለጽ ትክልል አይደለም፤ እኛን እንደሌለን ይቆጥራል፡፡ የሚል ነው፡፡ ከዚኽም በላይ "እኛነታችን ትተን ስለዐማራ ክብር እንድንሰብክ የሚያደርግ ነው፡፡" በሥንኙ አማካኝነት በክልሉ የሚኖሩትን ብሔረሰቦች በማግለል የዐማራነት ክብርና ደማቅ አርማ በመዝሙሩ እንዲጎላ በመደረጉ በፖለቲካና በኢኮኖሚ ተሳትፎ እንዲኹም የራስን ቋንቋ በመጠቀም፣ ባህልን በማክበር፣ በመጠበቅና በመግለጽ፣ በታሪክ የመኩራት ወዘተርፈ ልዩነት አለ ማለት አይቻልም፡፡

በሌላ በኩል፣ ከመዝሙሩ በተጠቀሰው ሥንኝ በተላለፈው መልእክት "አማራ ነኝ" ብሎ የሚያምነው የክልሉ ነዋሪ ምን ግንዛቤ አለው? ለሚለው ጥያቄ መልስ ከሰጡ ጥቂት ሰዎች መረዳት እንደሚቻለው፣ በመዝሙሩ ዐማራን ከፍ አድርጎ የሚገልጽ፣ በክልሉ የሚኖሩትን ዐማራ ያልኾኑ ብሔረሰቦች ስለማግለሉ ግንዛቤ የለም፡፡ የዐማራ ክብርና ደማቅ ዐርማ በመዝሙሩ ጎልቶ እንዲስተጋባ በመደረጉ ዐማራነት ከሌሎቹ የክልሉ ነዋሪዎች ተለይቶ ከፍ እንዲል አድርጓል፤ ዐማራ ያልኾኑትን ደግሞ አሳንሷል ተብሎ አይታሰብም፣ አይታመንም፡፡ ከዚኽም በላይ "የአማራነትን ክብር -ደማቅ አርማ ይዘን" በሚለው ሥንኝ የተገለጸው ሐሳብ ክልሉን የሚመራው የፖለቲካ ድርጅት አፋዊ ወይንስ በእውነተኛ አቋም ነው? ለዚኽ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ መዝሙሩ አገልግሎት እንዲሰጥ ያደረገውን የፖለቲካ ድርጅት አቋም ለመረዳት ያስችላል፡፡ የፖለቲካ ድርጅቱን (የብአዴንን) አቋም የዐማራን ሕዝብ "ሰፊው ሕዝብ"፣ "ዴሞክራሲዊ"፣ "ነፍጠኛ"፣ "ትምክህተኛ" እና "ቢሮክራት" (ፅናት፣ 1998) በማለት መከፋፈሉ አቋሙን ይገልጻል፡፡

---

[16] የሺዋስ ይስማው፣ ቃለ መጠይቅ፡፡
[17] አብጨ በየነ፣ ቃለ መጠይቅ፡፡
[18] ወ/ሮ አሰገድ ሚሪሳ፣ ቃለ መጠይቅ፡፡

ሰፊው ሕዝብ በሚል የሚጠራው የዐማራ ሕዝብ ክፍል ባለፉት ሥርዓቶች ተጎጂ የነበረና በለውጡ ተጠቃሚ ይኾናል ተብሎ በፖለቲካ ድርጅቱ ይታሰባል፡፡ ይኸ ሐሳብም በብሔረ ዐማራ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ/ብአዴን ፕሮግራም (1986፤2) "የአማራ ብሔር ሰፊ ሕዝብ በነፍጠኛው ስርዓትና የስርዓቱ ወኪሎች በሆኑት ከራሱ ብሔር ፈልቀው የራሱን ቋንቋ እየተናገሩ ሲገዙት የኖሩት ገዢዎች የደረሰበት ከብዝበዛና ጭቆና ሕዝቡን ለአስከፊ ኋላቀርነት፣ ለጠቅላላ ድኅነትና ጉስቁልና የዳረገ ነው፡፡" የብሔረ ዐማራ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ መጠሪያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ተልእኮ በመሸከም ለዐማራ "ሰፊ ሕዝብ" ጥቅም መታገሉን ይገልጻል፡፡ ይኽንንም በ፫ኛው ድርጅታዊ ጉባኤው ባፀደቀው የብአዴን ፕሮግራም ገጽ 11 ላይ "ባለፉት ዓመታት ሲታገልላቸው የነበሩትን የትግል አቅጣጫዎቹንም በመሠረቱ ከሰፊው የዐማራ ሕዝብ ጥቅም መጠናከር ጋር አዋሕዶ የሰፊው ሕዝብ ወገናዊነቱንም በአዲስ አቅጣጫዎቹ አማካይነት ይበልጥ አጠናክሮና አጉልቶ ይታገልላቸዋል፡፡" በማለት ይገልጻል፡፡ ዲሞክራሲዊ የሚባለው ዐማራ ደግሞ ለሰፊው የዐማራ ሕዝብ ጥቅም የሚደረገውን ትግል የሚደግፍና የራሱንም አስተዋጽኦ የሚያደርግ ነው፡፡ ይኽ የዐማራው ብሔር ክፍል በኢሕዴን/በብአዴን ክብር የሚሰጠው በመኾኑ በመዝሙሩ ክብሩና ዐርማው ደምቆ እንዲጠራ ተብሏል፡፡ ከዚኽ ብሔር ጥቅምና ክብር በተጻራሪ እንደቆሙ ተደርገው የተፈረጁት "ትምክህተኛ"፣ "ነፍጠኛ" እና "ቢሮክራት" በመባል የተፈረጁት ናቸው፡፡ "ትምክህተኛ" የሚባለው የዐማራ ኅብረተሰብ ክፍል በኢሕዴን በትምክህተኛ አስተሳሰብ ተፈረጀ ፡፡ የፖለቲክ ድርጅቱ ከኢሕዴን ወደ ብአዴን የተቀየረውም የትምክሕተኛውን አስተሳሰብ ለመታገልና ለመመከት ነው፡፡ "ትምክህተኛው የኅብረተሰብ ክፍል የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት (መዐሕድ)" የተባለ ድርጅት በማቋቋም የዐማራን ሕዝብ በዓላማው ዙሪያ ለማሰባሰብ የተደረገው ጥረት ኢሕዴን/ብአዴን እንደታገለው ከሚከተለው ጥቅስ እንረዳለን፡፡

> ትምክህተኞች በአንድ በኩል አማራ የሚባል ብሔር የለም እያሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉም ብሔረሰቦች ሲደራጁ አማራ የሚመራው ድርጅት አላገኘም የሚል ማደናገሪያ ለመፍጠር *"የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት (መአሕድ)"* የተባለ ድርጅት በማቋቋም የአማራን ህዝብ በትምክህተኛ አላማቸው ዙሪያ ለማሰባሰብ ቢጥሩም የአማራ ህዝብ "ሃቀኛ መሪ ድርጅት ኢህዴን ነው" ብሎ ከጎኑ ተሰለፈ፡፡ ይህንን ሁኔታ በጥሞና የገመገመው የኢህዴን አመራር ኢህዴን ህብረ ብሔራዊ አደረጃጀቱን መቀየርና የአማራ ብሔራዊ ደርጅት ሆኖ መደራጀት እንዳለበት ወሰነ (የብአዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት፣ 2008፤ 152)፡፡፡

በኢሕዴን "ዐማራ የለም" የሚለውን እንደ ትምክህተኛ አመለካከት የተቆጠረውን ሐሳብ በ1983 ዓ. ም. ከመለስ ዜናዊ ጋር ባደረጉት ውይይት የተናገሩት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ናቸው፡፡ ይኸ የትምክህተኛ አመለካከት ዐማራው በዐማራነቱ ሊያገኛቸው የሚገቡ ጥቅሞችን እንዳያገኝ የሚያደርግ ነው ብሎ ኢሕዴን በማመን የትምክህተኛን አመለካከት መታገል የፖለቲካ ድርጅቱ ኃላፊነት አድርጎ ቆጠረ፡፡ የፕሮፌሰሩን አመለካከት የሚጋራ ኅብረተሰብ ስለመኖሩ እርግጠኛ ባልተኾነበት እንዲያውም የሚተቿቸው ሰዎች በበዙበት አመለካከታቸውን ብዙ ተከታይ እንዳለውና የዐማራን ሕዝብ እንደሚጎዳ አድርጎ ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ ማዋል ትክክለኛውን የዐማራ ችግር አይፈታም፡፡

ነፍጠኛ (ነፍጥ ወይም ጠመንጃ የያዘ ወታደር) የቀድሞ ጊዜ ወታደር መጠሪያ ለዐማራ ብሔር አባላት ብቻ በመስጠትና ሌሎችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ይበድልና ይጨቁን እንደ ነበር ተደርጎ ከፍተኛ ፕሮፖገንዳ ተሠራበት፡፡ ይኸንንም ከሚከተለው የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ፕሮግራም (1986፡ 8-9) መረዳት ይቻላል፡፡

> ድርጅቱ ለ13 ዓመታት ትግሉን ያካሄደው በኅብረ- ብሔራዊ ድርጅት መልክ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ምንም እንኳን የቀድሞው ስርዓትና ገዢዎቹ የአማራውን ሕዝብ ሲረግጡትና ሲበዘብዙት የነበረ ቢሆንም በአማራው ሕዝብ ላይ ይደርስ የነበረው ጭቆና በብሔራዊ መልክ የተመሠረተ ስላልነበረ ነው፡፡ ይልቁንም የነፍጠኛው ሥርዓት በአማራው ብሔር ስም የሌሎቹን ብሔሮችና ብሔረሰቦች አፍኖና ረግጦ በመያዝ ብሔራዊ ጭቆና ያደርስባቸው ስለነበር፤ የአማራው ሕዝብ እንደሌሎቹ ብሔራዊ ጭቆና ሲደርስባቸው እንደነበሩት ብሔሮችና ብሔረሰቦች ብሔራዊ ጥያቄ አንስቶ የብሔር እኩልነትን የማስከበር ትግል ሊያካሂድ አይችልም ነበር፡፡ በብሔራዊ ጥያቄ መልክ የሚታገልለት ድርጅት መመስረትም የሕዝቡን ዋነኛ ጥያቄ የሚመለከት አልነበረም ፡፡

ከጥቅሱ መረዳት እንደሚቻለው "ነፍጠኛ" በሚል የተፈረጀው የዐማራው ኅብረተሰብ ክፍል በከተማም በገጠርም እንደሚኖርና ሌላውን ኅብረተሰብ ሲበድል እንደቆየ፣ የማይገባውን ጥቅም እንደያዘ ተደርጎ ተፈረጀ፡፡ በከተማ በተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚሠራው አማራ የሌሎች ብሔሮችን፣ ብሔረሰቦችን፣ ሕዝቦችን ድርሻ እንደያዘ በመቁጥር ከልዩ ልዩ መሥሪያ ቤቶች እንዲቀነስ ተደርጓል፡፡ በገጠር የሚኖሩ የገበሬ "ቢሮክራቶች" ኢህዴን ሥልጣን ከያዘ በኋላ በ1989 ዓ. ም. በዐማራ ክልል በተወሰኑ ዞኖች ውስጥ በተደረገው የመሬት ክፍፍል በደርግ የሥልጣን ዘመን በገበሬ ማኅበር አመራርነት የተሳተፉ ኹሉም ሰዎች አብሮ የሚኖረው ገበሬ ካገኘው መሬት ያነሰ መሬት እንዲሰጣቸው ተደርጓል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ መሬት ሲከፋፈል የገበሬ ማኅበር አመራር የነበሩ ሰዎች ሥልጣናቸውን ተጠቅመው ሰፊ መሬት ይዘዋል የሚል እምነት በድርጅቱ ተይዞ ስለነበር ነው (ፅናት፣ 1998)፡፡ ይኸ በሦስት ምክንያቶች ስሕተት ነው፡፡ አንደኛ "ኅብረተሰባዊነትን እከተላለኹ" ይል በነበረው የደርግ መንግሥት መሬት አስፍቶ ለመያዝ የሚያስችል ርዕዮተ ዓለማዊ መሠረት ስለአልነበረው የገበሬ ማኅበር አመራር የገበሬ ማኅበሩ አባላት ከተከፋፈሉበት መመሪያ በተለየ መሬት አስፍተው ከድርሻቸው የበለጠ መሬት ለመያዝ የሚችሉበት ዕድል ጠባብ ነበር፡፡ "የገበሬ ማኅበራት አመራር የነበሩ ገበሬዎች ድርጊቱን ፈጽመውታል" ከተባለም በጥናት ላይ ተመሥርቶ ውሳኔ ላይ መድረስ ሲገባ ኹሉንም በጅምላ ጥፋተኛ በማድረግ መሬታቸውን መቀነስና በአንድ ገበሬ ማኅበር ከሚኖሩ ገበሬዎች ከሚያገኙት የመሬት ድርሻ ቀንሶ መስጠት ተገቢነት የሌለው ድርጊት ነው፡፡

እንዲኽ ዓይነት አድሎ የተፈጸመባቸው ገበሬዎች በፖለቲካ አቋማቸው፣ በጠላትነት በመፈረጃቸው ብቻ ነው፡፡ ኹለተኛ ከሌሎች የገበሬ ማኅበር አባላት የበለጠ መሬት ይዘው ከተገኙ ቀንሶ በቤተሰባቸው ቁጥር እንደ ገበሬ ማኅበሩ አባላት እኩል መጠን መስጠት እየተቻለ አንድ ሄክታር (አራት ጥማድ) ብቻ እንዲሰጣቸው መደረጉ አድሎ ነው፡፡ ለሌሎች ገበሬዎች ግን

ከያዙት መሬት ውስጥ እስከ ሦስት ሄክታር መሬት እንዲይዙ ተፈቅዶላቸዋል፡፡ ሦስተኛ መሬት ይከፋፈል በነበረበት ጊዜ የገበሬ ማኅበር አባል ያልነበሩና ሥልጣናቸውን ተጠቅመው መሬት አስፍቶ ለመውሰድ ዕድል ያልነበራቸውን ገበሬዎች "የገበሬ ማኅበር አመራር ነበሩ" በሚል ስም አራት ጥማድ ብቻ መስጠቱ ኾን ብሎ በደል ከመፈጸም ውጭ ሌላ ትርጉም አይሰጠውም፡፡ ይኸም በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 25 ላይ የተደነገገውን የእኩልነት መብት የሚጻረርና ዜጎችን ከፋፍሎ የሚመለከት ኢ-ሕገ መንግሥታዊ ርምጃ እንደኾነ ይታመናል፡፡ ኢ-ሕገ መንግሥታዊ ውሳኔ እንደምንረዳው "የአማራነትን ክብር፣ ደማቅ አርማ ይዘን" የሚለው ሥንኘ እኩል መሬት ማግኘት መብት ያልተሰጠውን በዐማራ ክልል የሚኖረውን ገበሬ የሚመለከት አይደለም፡፡

በሌላ በኩል ነፍጠኛ ተብሎ የሚጠራው የዐማራ ኅብረተሰብ ክፍል ባለፉት ሥርዓቶች በገዥ መደብነት የሚፈረጅ፣ ወደ ተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች በመዝመት የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን መሬት የቀማ፣ ቋንቋቸውን ትተው አማርኛ ቋንቋ እንዲናገሩ ያስገደደ፣ ባህላቸውን የረገጠ፣ አካላቸውን ያጎደለ ተደርጎ ይቀርባል (ፅናት፣ 1998)፡፡ የግንባሩ አባል ድርጅት ኦሕዴድ ለነፍጠኛው "ጡት ቆራጭነት" አኖሌ ላይ፣ "ለጨፍጫፊነቱ" ደግሞ ጨለንቆ ላይ ሐውልቶች በመሥራት ዐማራው እንዲወገዝ፣ እንዲረገም ሲያደርግ ብአዴን በበኩሉ ሐውልት አስመረቀ እንጂ ይኽ ኹኔታ በሐሰት ትርክት ላይ የተመሠረተና የታሪክ እውነትነት የሌለው መኾኑን አልሞገተም፡፡ ለነፍጠኛው ዐማራ ጥፋት፣ ኃጢአት የተባለ ኹሉ ሲሰጠው ለከሳሾቹ መሰከረ እንጂ ይኽ ኹኔታማ ውሸት ነው አላለም፡፡ የኢትዮጵያ የገጠር መሬት ሥሪትና የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት በ1967 ዓ. ም. በወጡ በዐዋጆች (ዐዋጅ ቁጥር 31/1967 እና ዐዋጅ ቁጥር 47/1967) ቢለወጥም ዛሬም መሬት ነጣቂ፣ የከተማ ቦታ በትርፍ የያዘ ጠላት ተደርጎ ሲሰበክና በዚኽ ሰበብ በዐማራ ላይ ሲቀሰቀስና በሕይወት ያለ ድኻ ዐማራ ሲጎዳ የዐማራን ክብር ማስጠበቅ ቀርቶ በሕይወት የመኖር ሰብአዊ መብቱን ሲያጣ፣ የአካል ጉዳት ሲፈጸምበት፣ የሥነ ልቦና ጥቃት ሲደርስበት ስለዐማራ ክብር የሚዘምረውና የሚያዘምረው የክልሉ መንግሥት ጆሮውን ነፍጎታል፡፡ በገባሪና አስገባሪ መካከል በነበረው ግንኙነት አስገባሪው ዐማራ ብቻ እንደ ነበር ሲሰበክ መስካሪው ብአዴን/ኢሕዴን ነው፡፡ የገባሪና አስገባሪ ግንኙነት በዐዋጅ ከተሻረ ቢቆይም ዐማራ የኾነ ኹሉ ያልፈጸመውን እዳ እንዲከፍል ሲደረግ የጥፋት ወራሽ ተደርጎ ሲቆጠርና የበቀል ጥቃት ሲፈጸምበት ብአዴን ድርጊቱን በተዘዋዋሪም፣ በቀጥታም ለማስቆም ያደረገው ጥረት የለም፡፡

በ1967 ዓ. ም. በዐዋጅ የተሻረው የገባሪና የአስገባሪ ግንኙነት ዐማራው ብቻ ተጠያቂ ሲደረግ "ለዐማራው ቆሜአለኹ" የሚለው ብአዴን/ኢሕዴን "እውነት" አለ እንጂ የሐሰት ውንጀላ ስለመኾኑ በተለያዩ ክልሎች የሀገሪቱ በሚፈቅደው መሠረት ራሱን በራሱ ማስተዳደር፣ በቋንቋው መጠቀም ወይም መዳኘት፣ በመንግሥት የሥልጣን እርከን ውክልና የለውም፡፡ ከዚኽም በላይ በማንኛውም የሀገሪቱ ክፍል ተዘዋውሮ የመሥራት፣ ንብረት የማፍራት መብቱ የተገደበ ነው፡፡ ንብረቱን ተቀምቶ፣ ከመኖሪያ ቀየው፣ ይባረራል፤ ልዩ ልዩ የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብት ጥሰት ይፈጸምበታል፤ ይደበደባል፣ የአካል ጉዳት ይደርስበታል፣ ይገደላል፡፡ ይኽም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት መግቢያ፣ "መጪው የጋራ ዕድላችን መመስረት ያለበት ከታሪካችን የወረስነውን የተዛባ ግንኙነት በማረምና የጋራ ጥቅማችንን

በማሳደግ ላይ መኾኑን በመቀበል ነው፡፡" በማለት ተገልጿል፡፡ የዐማራ ክልል ሕዝብ የወደፊት የጋራ መልካም ሕይወት ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ጋራ የተቆራኘ መኾኑ በዐማራ ክልል ሕገ መንግሥት (1994) መግቢያ ላይ "መላ የአገራችን ብሔረ-ብሔረሰቦችና ህዝቦች ለዘመናት ባካሄዱት አኩሪ ተጋድሎ የነበረው ኋላ ቀርና አፋኝ ሥርዓት ተገርስሶ አገራችን ኢትዮጵያ የግለሰቦችና የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ጨምሮ የኹሉም ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች በሙሉ የተከበሩባትና በአጠቃላይ የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ መኾኗ ለጋራ ዕድገታችን መፋጠን ያለውን ጠቀሜታ በመገንዘብ" መኾኑ ተገልጿል፡፡

በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 32 (2) ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በመረጠው የሀገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመሥረት ነፃነት እንዳለው ቢደነገግም በተለያዩ ክልሎች የሚኖር ዐማራ የግለሰብም፣ የቡድንም ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቹ አይከበሩም፡፡ በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥትም፣ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትም በአርባጉጉ፣ በበደኖ፣ በወልቃይት፣ በመተከል፣ በምሥራቅ ወለጋ፣ በጉራፈርዳ ወዘተርፈ የሚኖር የዐማራ ብሔር አባል መሬቱን ተነጥቋል፤ ታስሯል፤ ተፈናቅሏል፤ ተገድሏል (ሙሉቀን፣ 2008)፡፡ የዐማራ ክልል መንግሥት ከየክልሎቹ አመራሮች ጋር በመነጋገር ችግሩን አልፈታም፤ ጥፋተኞቹ ወደ ሕግ እንዲቀርቡ፤ ተጎጂው ካሣ እንዲያገኝ አላደረገም፡፡ "መጤ" እየተባለ ለዘመናት ከኖረበት ሲፈናቀል፤ የብሔረሰብ ተዋጽዖ ለማመጣጠን በሚል ሽፋን ከሚሠራበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሲባረር ኢሕዴን/ብአዴን "ለምን?" ብሎ ሊጠይቅ ቀርቶ ራሱ መመሪያ አውጪም፣ አስፈጻሚም፣ ፈጻሚም ነበር፡፡ ዐማራው የተገደለው፣ ከመኖሪያ ቀየው የተፈናቀለው፣ የሌላውን መሬት ስለነጠቀ፣ ባህሉን ስለአጠፋፉ ፣ ቋንቋውን እንዳይናገር ስለከለከለ ሳይኾን በሐሰት ትርክትና በፀረ-ዐማራ ቅስቀሳ ነው፡፡

በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 38 (1) (ሀ-ሐ) ላይ በግልጽ እንደተደነገገው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በቀለም፣ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ላይ የተመሠረተ ልዩነት አይደረግበትም በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚኽ ድንጋጌ መሠረት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሀ) በቀጥታ እና በነፃነት በመረጣቸው ተወካዮች አማካኝነት በሕዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ መብት አለው፡፡ ለ) ዕድሜው ፲፰ ዓመት የሞላው ሰው በሕግ መሰረት የመምረጥ መብት አለው፣ ሐ) መራጩ ፈቃዱን በነፃነትና በምስጢር ድምፅ አሰጣጥ የሚገልጽበት በማናቸውም የመንግሥት ደረጃ በየጊዜው በሚካሔድ ምርጫ የመመረጥና የመምረጥ መብቶች አሉት፡፡ ይኹን እንጂ በየትኛውም ክልል የሚኖር ዐማራ የመምረጥ እንጂ በዕጩነት ቀርቦ የመመረጥ መብት የለውም፡፡ በመጀመሪያ ዐማራው በሚኖርበት ክልል መልክዓ ምድር የነዋሪነት መብት እንደማይከበርለት በአንዳንድ የክልል ሕገ መንግሥታት ተደንግጓል፡፡ ለምሳሌ፣ በተሻሻለው የቤኒሻጉል-ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት አዋጅ ቁጥር 31/1995 አንቀጽ 2 "በክልሉ ውስጥ የሚኖሩ ሌሎች ሕዝቦች የሚታወቁ ቢሆንም የክልሉ ባለቤት ብሔረሰቦች በርታ፣ ጉሙዝ፣ ሽናሻ፣ ማኦና ኮሞ

ናቸው፡፡" በማለት ተደንግጓል፡፡[19] የክልሉ "ባለቤት" ከተባሉት ሕዝቦች መካከል ኮም [ኮሞ]፣ ሰሜን ማኦ [ማኦ] እና ሽናሻ የራሳቸውን የወረዳ አስተዳደር መመሥረት እንደማይችሉ በአዋጅ ቁጥር 7/1984 አንቀጽ 3 (2) (ሀ) ተደንግጎ ነበር፡፡ ብሔራዊ ክልላዊ የሽግግር መስተዳድሮችን ለማቋቋም በወጣው ዐዋጅ ቁጥራቸው አነስተኛ በመኾኑ የወረዳ አስተዳደር መመሥረት እንደማይችሉ ተደንግጎ ነበር፡፡ ይኹን እንጂ በክልሉ ሕገ መንግሥት የቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልል መንግሥት ባለቤትነታቸው ተደንግጓል፡፡ በመተከል ዞን በተለይም ፓዊ አካባቢ የሚኖሩ የአማራና የአገው ተወላጆች በአማራ ክልል ሥር ለመተዳደር ተደጋጋሚ ጥያቄ አቅርበው አልተፈቀደላቸውም፡፡ በሽግግሩ ወቅት አቶ ታምራት ለዓይኔ ግፊት የቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልል መንግሥት የልዩ ወረዳ አስተዳደር እንዲያደራጁ ፈቅዶላቸው ራሳቸውን በራሳቸው ለጥቂት ዓመታት ካስተዳድሩ በኋላ የዐማራ ተወላጆቹ የክልሉ ባለቤት ስለአልኾኑ ወይም እንደ "መጤ"ስለ ተቆጠሩ የልዩ ወረዳ አስተዳደር ሊኖራቸው አይችልም በማለት የተፈቀደላቸውን መብት ከ2002 ዓ. ም. ጀምሮ እንዲያጡ ተደርጓል፡፡[20] በተሻሻለው የጋምቤላ ክልል ሕገ መንግሥትም ተመሳሳይ የኾኑ ድንጋጌዎችን በማካተት የዐማራ ሕዝብ በክልሉ ፖለቲካዊና አስዳደራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዳይኾን አድርጓል፡፡ በተመሳሳይ ኹኔታ በተሻሻለው የሐረሪ ሕገ መንግሥት አዋጅ ቁጥር 46/1997 አንቀጽ 8 "የሐረሪ ህዝብ የክልሉ የበላይ ስልጣን ባለቤት ሲሆን፣ የሕዝቡ የበላይነትም የሚገለጸው በዚህ ህገ-መንግስት መሰረት በሚመርጣቸው ተወካዮችና ራሱ በሚያደርገው ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ነው፡፡" ይላል፡፡ ይኹን እንጂ በሐረሪ ክልል የሚኖረው የዐማራ ቁጥር በሕገ መንግሥቱ የክልል ባለቤት እንደኾነ ከተደነገገው የሐረሪ ሕዝብ ከሦስት እጥፍ በላይ ይበልጣል (Office of Population and Housing Census Commission Central Statistical Authority, 1999:34)፡፡

እንደዚኹም በኦሮሚያ ክልል የሚኖረው የዐማራ ቁጥር ከኹለት ሚሊዮን እንደማያንስ፣ የክልሉ ሥልጣን ባለቤት የኦሮሞ ሕዝብ መኾኑን በተሻሻለው የኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግሥት አዋጅ ቁጥር 46/1994 አንቀጽ 8 "የኦሮሞ ሕዝብ የክልሉ መንግሥት የበላይ ሥልጣን ባለቤት ሲሆን የህዝቡ የበላይነትም የሚገለጸው በሚመርጣቸው ተወካዮችና ራሱ በቀጥታ በሚያርገው [በሚያደርገው] ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ነው፡፡" በማለት ይደነግጋል፡፡ በተሻሻለው የኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግሥት አዋጅ ቁጥር 46/1994 አንቀጽ 5 የክልሉ የሥራ ቋንቋ በተመለከተ "አፋን

[19]እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1994 ከወጣው የክልሉ የሕዝብና የቤት ቆጠራ ውጤት መረዳት እንደሚቻለው የክልሉ ባለቤቶች የተባሉት ሕዝቦች የእያንዳንዳቸው ብዛት ሲታይ ጀበላዊ [በርታ] 115,602፣ ጉሙዝ 107,495፣ ሺናሻ 32105፣ ማኦ 2,732 እና ኮሞ 1,109 ነው፡፡ በክልሉ 102061 ዐማራ፣ 58,833 ኦሮሞ እና 17,545 አገው ቢኖሩም ከፖለቲካ የተገለሉ ናቸው፡፡ (Office of Population and Housing Census Commission Central Statistical Authority, 1999:37)፡፡

[20] ይኽ ሲሳይ መንግሥቴ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፌዴራሊዝም ጥናት የትምህርት ክፍል መምህር፣ አዲስ አበባ፣ ጥር 18 ቀን 2013 ዓ. ም. የሰጡት ቃለ መጠይቅ ነው፡፡
ከዐማራ ክልል ጋር የሚዋሰነውን ፓዊ በልዩ ወረዳነት ለቤንሻንጉል-ጉሙዝ ተጠሪ ከማድረግ ይልቅ ወደ ዐማራ ክልል አለመከለሉ የኢህዴን/ብአዴንን ድክመት ይገልጻል፡፡ በመተከል ዞን በዐማራና በአገው ተወላጆች ላይ የሚፈጸመው የሰብአዊ መብት ጥሰት ትናንት የፖለቲካ ድርጅቱ የፈጸመው ኃላፊነት የጎደለው ሥራ ውጤት ነው፡፡ በወልቃይት፣ በጠገዴ፣ በጠለምትና በራይ የሚኖረው ዐመራ ወደ ትግራይ የተከለለው፣ እንዲሁም በደራና በጃርሶ የሚኖረው ዐማራ ወደ ኦሮሚያ እንዲካለል የተደረገው የኢህዴን/ብአዴን ስምምነት ሳይኖርበት አይደለም፡፡ በዐማራና በኦሮሞ መካከል ዐባይን የተፈጥሮ ወሰን ሰደረግ፤ በዐማራና በትግራይ መካከል ላለው ድንበር ተከዜ ወንዝ አለመመረጡ አንድ ዓይነት አሠራር አለመኖሩን ያስረዳል፡፡

አሮሞ የክልሉ መንግሥት የሥራ ቋንቋ ይሆናል፤ የሚጻፈውም በላቲን ፊደል ነው፡፡" በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚኽ ድንጋጌ መሠረትም በክልሉ የሚኖረው ዐማራ ቋንቋውን ለተለያዩ ጉዳዮች አይጠቀምም፡፡ ማንኛውም ኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ በቋንቋው የመናገር፣ የመጻፍ፣ ቋንቋውን የማሳደግ እና ባህሉን የመግለጽ፣ የማዳበርና የማስፋፋት እንዲኹም ታሪኩን የመንከባከብ መብት እንዳለው የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 (2) ይደነግጋል፡፡ እንዲኹም በአንቀጽ 39 (3) እንደተደነገገው ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ ራሱን የማስተዳደር ሙሉ መብት አለው፡፡ ይኽ መብት ብሔሩ፣ ብሔረሰቡ፣ ሕዝቡ በሰፈረበት መልክዓ ምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋም እንዲሁም በክልልና በፌዴራል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብትን እንደሚያጠቃልል ቢደነግግም በተለያዩ ክልሎች ለሚኖረው ዐማራ መብቶቹ የተነፈጉ ናቸው፡፡ ዐማራው በሚኖርበት ክልል ራሱን በራሱ የማስተዳደር ሕገ መንግሥታዊ መብት ተነፍጎት በክልሉ መዝሙር "ከሌሎች ሕዝቦች ጋር እኩል ተከባብረን" የሚል ስንኝ በመዝሙሩ ማካተት ወደ ሕዝቡ የሚደርስ እውነትን አያንፀባርቅም፡፡

በየክልሎቹ ዐማርኛ ተናጋሪው በራሱ ቋንቋ እንዲማር፣ ራሱን በራሱ እንዲያስተዳድር በየክልሎቹም ዐማራው ቋንቋውን በትምህርት ቤት፣ በአስተዳደር፣ በፍርድ ቤት የመጠቀምና የማሳደግ መብት የለውም፡፡ ጋዜጣና መጽሔት አያሳትምም፤ ማስታወቂያ አይነግርም፣ በሬዲዮና ቴሌቪዥን ባህሉንና ታሪኩን አይገልጽም፣ አይዘግብም፡፡ በተሻሻለው የሶማሌ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት አዋጅ ቁጥር ፲፰ሀ፲፱፻፺፬ [፲፰/፲፱፻፺፬] አንቀጽ 6 "የክልሉ መንግሥት የሥራ ቋንቋ ሶማልኛ ነው፡፡" በማለት ይደነግጋል፡፡ እንደዚኹም ተሻሽሎ በወጣው የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት አዋጅ ቁጥር 45/1994 አንቀጽ 5 (2) "ትግርኛ የትግራይ ብሔራዊ ክልል መንግስት የስራ ቋንቋ ይሆናል፡፡" በማለት ይደነግጋል፡፡ በክልሉ ሕገ መንግሥት መኖራቸው ዕውቅና የተሰጣቸው የኩናማና የሳሆ ሕዝቦች በቋንቋቸው የመማር፣ ቋንቋቸውን የማሳደግ መብታቸው በአንጻራዊነት ተከብሯላቸዋል ማለት ይቻላል፡፡ በክልሉ የመገናኛ ብዙኃን (ቴሌቪዥንና ሬዲዮ) በቋንቋቸውን ዜናዎችን ይዘግባሉ፤ ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን ያቀርባሉ፡፡ እነዚኽ ሕዝቦች ቁጥራቸው አነስተኛ ነው በሚል በሽግግሩ ወቅት በአዋጅ ቁጥር 7/1984 አንቀጽ 3 (2) (ሀ) የወረዳ አስተዳደር ማቋቋም እንደማይችሉ መደንገጉ ይታወቃል፡፡ ከእነዚኽ ሕዝቦች በቁጥር የሚበልጥ ዐማራ በክልሉ ቢኖርም[21] በክልሉ ሕገ መንግሥት ዕውቅና አልተሰጠውም፡፡ በእዚኽ ክልል የሚኖረው የዐማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ቋንቋውን በትምህርት ቤት የመጠቀም መብት አልተሰጠውም፡፡ ቋንቋውን የማሳደግና በመገናኛ ብዙኃን አማካኝነት የመጠቀም መብት አልተፈቀደለትም፡፡ የአስተዳደር ሥራዎችንና የፍርድ ቤት ኺደቶችን በቋንቋቸው አይጠቀምም፡፡ በአጠቃላይም ሲታይ በተለያዩ ክልሎች ውስጥ የሚኖረው ዐማራ ባህሉን የመግለጽ፣ የማዳበርና የማስፋፋት፤ እንዲኹም ታሪኩን የመንከባከብ መብት የለውም፡፡ በሚኖርበት መልክዓ-ምድር

[21]በOffice of Population and Housing Census Commission Central Statistical Authority (1998:37) እንደተገለጸው በትግራይ ክልል ከሚኖረው ሕዝብ መካከል ዐማራው 81, 297 ነው፡፡ የሳሆ ብሔረሰብ 22, 297 ሲኾን ኩናማ ሕዝብ ደግሞ 1, 819 ነው፡፡ ይኹን እንጂ፣ በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 የትግራይ ብሔር፣ የኢሮብ (ሳሆ) እና የኩናማ ብሔረሰቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለው መብት የተጠበቀ መኾኑ ተደንግጓል፡፡

መንግሥታዊ ተቋማትን በማቋቋም ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብት አልተሰጠውም፡፡ የወረዳ፣ የዞን አስተዳደርና የክልል ምክር ቤት ውክልናም የለውም፡፡ ይኸም ዐማራው ከሌሎች ኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ጋር በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ የመኖር መብቱ አልተከበረለትም፡፡ በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9 (2) ማንኛውም ዜጋ፣ የመንግሥት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሌሎች ማኅበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው ሕገ መንግሥቱን የማክበርና ለሕገ መንግሥቱ ተገዢ የመኾን ኀላፊነት እንዳለባቸው ቢደነገግም ተግባራዊ አለመደረጉን ቀደም ሲል ከተደረገው ማብራሪያ መረዳት ይቻላል፡፡ የተጠቀሰውን የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት ድንጋጌ ማስከበር የሚመለከታቸው የየክልሎቹ አካላት ኀላፊነት ቢኾንም የዐማራ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ በዐማራው ስም የተደራጀውና የዐማራን ክልል በበላይነት የሚመራው ብአዴን የበለጠ ኃላፊነት አለበት፡፡ ይኸንን ኃላፊነቱን በተግባር ሲተገብር የታየበት ጊዜ ግን የለም፡፡

በተለያዩ ክልሎች ከሚኖረው ዐማራ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች አለመከበር፣ ከፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያና ማኅበራዊ ሕይወት መረዳት እንደሚቻለው በተጠቀሰው የመዝሙሩ ሥንኝ የተላለፈው መልእክት በሌሎች ክልሎች የሚኖረውን ዐማራ አይመለከትም፡፡ በተለያዩ ክልሎች የሚኖረው ዐማራ የመመረጥ መብት ስለሌለው በየትኛውም የመንግሥት የሥልጣን ደረጃ የመወከል መብት የለውም፡፡ በየትኛው ክልል የሚኖር ዐማራ ራሱን በራሱ የማስተዳድር መብት የለውም፡፡ በትግራይ፣ በኦሮሚያ፣ ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ በሐረሪ ሕዝብ፣ በሶማሌና በአፋር ክልሎች የሚኖረው ዐማራ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቹ እንዲከበሩ አልተደረገም፡፡ በተለያዩ ክልሎች የሚኖረው ዐማራ ሲገደል፣ የአካል ጉዳት ሲፈጸምበት የዐማራ ክልል መንግሥት ጥቃቱ እንዳይደርስበት ያደረገው ጥረት የለም (ሙሉቀን፣ 2008፤ ቹቹ፣ 2011)፡፡ በጥቃት ፈጻሚዎች ላይ ሕጋዊ ርምጃ እንዲወሰድ ወይም ለፍትሕ እንዲቀርቡ አላደረገም፡፡ "ክልላችንን ለቅቀኽ ውጣ" በማለት ንብረት አፍርቶ ከሚኖርበት ክልል እንዲፈናቀል የተደረገው ዐማራ ብዙ ነው፡፡ ስለኾነም፣ ብአዴን በተለያዩ ክልሎች የሚኖረውን ዐማራ ሰብአዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶች እንዲከበር ሳይደረግ ክብሩ ከፍ እንዲል፣ አርማው እንዲጎላ በክልሉ መዝሙር እንዲንፀባረቅ ማደረጉ አፋዊ ከመኾን የዘለለ ዋጋ የለውም፡፡ "ሰፊው የአማራ ሕዝብ" በማለት የተጠራው በክልሉና ከክልሉ ውጭ ለሚኖረው ዐማራ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሳይከበሩ በሌሎች ክልሎች በሚኖሩት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሊከበር የሚችል ክብርና ዐርማ ይኖረዋል ተብሎ አይታሰብም፡፡

"ከሌሎች ሕዝቦች ጋር - እኩል ተከባብረን" የሚለው ሥንኝ ዐውዳዊ ትርጉም የዐማራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ጋራ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በእኩልነትና በመከባበር አብሮ ለመኖር ያለውን እምነት ይገልጻል፡፡ የዐማራው ሕዝብ ሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦችን እንደሚያከብረው ኹሉ፣ ሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦችም የዐማራን ሕዝብ እንዲያከብሩ መዝሙሩ ይጠይቃል፡፡ የዐማራው ሕዝብ የሌሎችን ብሔር-ብሔረሰቦች ሰብአዊ መብት፣ ባህል፣ ታሪክ፣ ቋንቋ፣ በየራሳቸው መልክዓ ምድራዊ አሰፋፈር ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ፣ የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን መብታቸውን ሲያከብር፣ በተመሳሳይ ሌሎችም የዐማራውን መብቶች በማክበር በፍቅር ላይ የተመሠረተ ዘላቂ አንድነት እንደሚኖራቸው

መዝሙሩ "በፍቅር በአንድነት - አብረን እንዘልቃለን" በማለት ይገልጻል፡፡ የዐማራ ሕዝብም ሌሎች የኢትዮጵያ ብሔሮችም፣ ብሔረሰቦችም፣ ሕዝቦችም በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ የመኖር እምነታቸው ምክንያት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይኸውም፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ሰላም፣ ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ ለማስፈን፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦችን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት ለማፋጠን፣ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት በመጠቀም በነጻ ፍላጎት፣ በሕግ የበላይነትና በራስ ፈቃድ የተመሠረተ አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ በጋራ ለመገንባት ነው፡፡ በተጨማሪም፣ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የየራሳቸው አኩሪ ባህል፣ የየራሳቸው መልክዓ ምድራዊ አሰፋፈር ያላቸው፣ በተለያዩ መስኮችና የግንኙነት ደረጃዎች ተሳስረው አብረው የኖሩና የሚኖሩ፣ ያፈሩት የጋራ ጥቅምና አመለካከት አለን ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ ስለኾነም፣ ጥቅማቸውን፣ መብታቸውንና ነጻነታቸውን በጋራ እና በተደጋጋፊነት ለማሳደግ አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ የመገንባትን አስፈላጊነት በማመን በጋራ የመኖር እምነት እንዳላቸው በመዝሙራቸው ማንጸባረቃቸው ሕገ መንግሥቱን መሠረት ያደረገ ነው፡፡

### 2.3) የዐማራ ክልል ሕዝብ የጋራ ዕድል በመዝሙሩ መንፀባረቁ

መዝሙሩ "የክልሉን ሕዝብ የወደፊት የጋራ ዕድል የሚያንፀባርቅ" እንዲኾን በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 4 ተደንግጓል፡፡ በዚኽ ድንጋጌ "ሕዝብ" በሚለው የወል መጠሪያ የተጠሩት በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 39 (1-3) ተደጋግሞ የተጠራው አማራና በአንቀጽ 39 (6) እና በአንቀጽ 45 (2) የኽምራ፣ የአዊና የኦሮሞ ብሔረሰቦች ተብለው የተጠሩት እንዲኹም በአንቀጽ 45 (5) "በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች ብሔር-ብሔረሰቦችና ሕዝቦች" በማለት የተገለጹት ናቸው፡፡ "የወደፊት የጋራ ዕድል" የሚለውም በዐማራ ክልል ብሔር-ብሔረሰቦች ወደፊት የሚኖራቸውን የወል ዕጣ ፈንታ ይገልጻል፡፡ ይኽም የክልሉ ብሔር-ብሔረሰቦች ዕድላቸው የተሳሰረ ነው፡፡ በአንድ ብሔረሰብ ላይ የሚደርሰው በጎም ኾነ መጥፎ ነገር ለሌሎቹ ብሔረሰቦች ይተርፋል ወይም በአንዱ የሚደርሰውን ከሌሎቹ ብሔረሰቦች ነጥሎ መመልከት አይቻልም ማለት ነው፡፡ ይኽንን እውነታ የክልሉ መዝሙር ማንጸባረቅ ወይም መንገር እንዳለበት የክልሉ ሕገ መንግሥት ይደነግጋል፡፡

የዐማራ ሕዝብ የወደፊት የጋራ ዕድል የሚለው አዎንታዊ የኾነን ስሜት ይገልጻል፡፡ ይኸውም የዐማራ ሕዝብ በተለያየ የሕይወት መስክ ሊያገኝ የሚችለውን መልካም ነገር ይጠቁማል፡፡ የጋራ ዕድል የሚለው ሐረግ ዐውዳዊ ትርጉም ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ማኅበራዊ መብቶች መከበር የብሔር-ብሔረሰቦችን የጋራ ዕድገት ያፋጥናል፡፡ ክልሉ በሕገ መንግሥት ብቻ እንዲመራ ማድረግ፣ የሕግ የበላይነት ማስፈንና የክልሉን መንግሥት ማጠናከር፤ ማጎልበት፤ የጋራ ዕድገትን ያፋጥናል፡፡

በክልሉ መዝሙር የመጀመሪያ ሥንኝ የዐማራ ክልል "የታሪክ ማኅደር" ነው፤ የክልሉ ብሔር-ብሔረሰቦች የዳበረ የታሪክ ሀብት አላቸው ማለትን ይገልጻል፡፡ ታሪክ በጊዜ ቅደም ተከተል የተፈጸመ፣ ያለፈ የሕዝብ(ቦች)ን፣ የመንግሥታትን፣ የመሪዎችን ድርጊትና ኹኔታ የሚዘረዝርና

በጽሑፍ የሚገለጽን ወይም በቃል የሚነገርን፣ ወይም በዐይን የሚታይንና በእጅ የሚዳሰስን ሥነ ቅርፅ፣ ኪነ ሕንፃ፣ ሥነ ሥዕልና ሥነ ጽሑፍ ይገልጻል፡፡ በመዝሙሩ ታሪክ የሚለው ቃል የሚገልጸው በክልሉ የሚገኙትን የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፣ የጎንደር አብያተ መንግሥታትና አብያተ ክርስቲያናት መኾኑን የክልሉን ዐርማ ለመወሰን የወጣው መመሪያ ያስረዳል (የዐማራ ብሔራዊ ክልል መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ 1985-1992)፡፡ ማኅደር በውስጡ መጽሐፍ ወይም ሌላ ነገር ለመያዝ፣ ለማስቀመጥ የሚያገለግል ከቆዳ ወይም ከሌላ ነገር የተበጀ ባለማንጠልጠያ ዕቃ ነው፡፡ ማኅደር ከለሰለሰና ከጠንካራ ቆዳ/ጨርቅ መዘጋጀቱ የዕቃውን ጥራትና ጥንካሬ ይገልጻል፡፡ በውስጡ የሚቀመጠውም መጽሐፍ ውድና ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ዕቃ ነው፡፡ የዐማራ ክልል በውስጡ ለሥራ፣ ለለውጥ፣ ለተሻለ ነገር የሚተጋና የሚፍጨረጨር ሕዝብ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የሕዝብ፣ የመንግሥት፣ የመሪዎች በጊዜ ቅደም ተከተል የተፈጸመ/የተከወነ የሚዘረዘር፣ የሚጠናና የሚገለጽ ድርጊት የተከወነበት ክልል ነው፡፡ የዐማራ ክልልም የሚወደድ፣ የሚመረጥ ክልል፣ ብሔር-ብሔረሰቦቹ የሚከበሩ፣ የሚወደዱ መኾናቸውን፣ ታሪካቸውም የሚኮራበት፣ የሚመኩበት በአለኝታነት የሚያዝ ነው ማለትን ይገልጻል፡፡ ማኅደር የሚለው ቃል ዐውዳዊ ፍቺውም በክልሉ የተለያዩ ታሪኰችና የታሪክ ማስረጃዎች መኖራቸውን ይነግራል፡፡ ታሪኰቹና የታሪክ ማስረጃዎቹም በክልሉ የሚኖሩት የኹሉም ብሔር-ብሔረሰቦች መኾኑን "የታታሪ ሕዝቦች" የሚለው የመጀመሪያው ሐረግ ይገልጻል፡፡ በጽሑፍ የሰፈረውና በቃል የሚነገረው ታሪክ ትውልድ እንዲኰራበት ያደርጋል፤ በዐይን የሚታየው፣ በእጅ የሚዳሰሰው ኪነ ሕንፃ፣ ሥነ ሥዕል፣ ሥነ ቅርፅ፣ ሥነ ጽሑፍ ወዘተርፈ በታሪክነቱ የትውልድ ኩራትንና በራስ የመተማመንን ግንዛቤ ያዳብራል፡፡ በቱሪስት መስኅብነቱም የገቢ ምንጭ ኾኖ እንደሚያገለግል ግንዛቤ ይፈጥራል፡፡

"የአኩሪ ባህል አምባ" በሚለው ሐረግ "አኩሪ" የሚለው ቅጽል "ባህል ዐምባ" የሚለውን ስማዊ ሐረግ ይገልጻል፡፡ በግጥሙ ውስጥ ባለው ዐውዳዊ አገልግሎት፣ ባህል[22] የሚለው ቃል የክልሉ ሕዝቦች የየራሳቸው የአኗኗር ዘዴ፣ የጋብቻ ሥርዓት፣ ወግ፣ ልማድ፣ ትውፊት፣ ደንብ፣ ፎክሎር ወዘተርፈ አላቸው ማለት ነው፡፡ ዐምባ በአንድ አካባቢ መሰባሰብን፣ መከማቸትን፣ መገኘትን ይገልጻል፡፡ "ባህል ዐምባ" የሚለው ስማዊ ሐረግ የተለያዩ ባህሎች ተከማችተው የሚገኙበት ክልል ማለት ነው፡፡ ክልሉም የዐማራ ክልል ነው፡፡ የባህል ሀብት ያላቸው ሕዝቦች በማንነታቸው ይኰራሉ፡፡ በመዝሙሩ የክልሉ "ሕዝቦች" አኩሪ የባህል ባለቤቶች መኾናቸውን መግለጽም ሥነ ልቦናዊ ጠቀሜታ አለው፡፡ በራስ መተማመንን ከፍ ያደርጋል፡፡ በመዝሙሩ በክልሉ ሀብትነት የተቆጠረው "ድንግል አፈር" ገና ያልተበላና ያልተሟጠጠ ለግብርና ሥራ፣ ለከብት እርባታና ለማዕድን ቁፋሮ የሚያገለግል መሬት ባለቤትነትን ይገልጻል፡፡ ድንግል መሬት በደን የተሸፈነ፣ ለዱር እንስሳትና ለአእዋፋት መጠለያነት የሚያገለግል፣ የማይነጥፍ ውሃ ያለበት ማለትም ነው፡፡

[22]ባህል የሚለው ቃል ሰፊ ጽንሰ ሐሳብን የሚገልጽ ከመኾኑም በላይ በተለያዩ የባህል ባለሙያዎች ስምምነት ላይ የተደረሰበት ብያኔም አልተሰጠውም፡፡ በሀገራችንም የተለያዩ ኅብረተሰቦችን ባህል በማጥናት የተሰጠ ብያኔ ማግኘት አልተቻለም፡፡ ስለኾነም፣ በዚኽ ጥናት ባህል የሚለውን ቃል ለመረዳት የተሞከረው በደስታ (1962) እና በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል (1993) መዛግብተ ቃላት የተሰጡትን ፍቺዎች መነሻ በማድረግ ነው፡፡ ይኽም ኾኖ፣ ለቃሉ መፍቻ ተብለው የተደረደሩት ቃላት ተጨማሪ ፍቺ የሚጠይቁ እንደኾኑ ይታመናል፡፡

[23] የድንግል መሬት ባለቤት መኾንም ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚረዳ፣ የሀገር ሀብት መኖርን ያስረዳል፡፡ ይኽም በራስ መተማመንን ያጎለብታል፤ የኑሮ ተስፋም ይፈጥራል፡፡ ብሩህ ተስፋ የመኖሩን እምነትም "የሕዝቦችሽ[24] ተስፋ-ለሟ ክልላችን" በሚለው ሥንኝ ተገልጿል፡፡ የክልሉ ሕዝቦች ተስፋ እንዲመሠረት የተደረገውም በሕዝቡ ታታሪነት በክልሉ ለምነትና በውስጡ ባሉ ሰው ሠራሽና ባልተበላው የተፈጥሮ ሀብት ላይ ነው፡፡

በመዝሙሩ የክልሉ "ሕዝቦች" ተስፋ የተመሠረተው ሰላም በሰፈነበት፣ ፍትሕ በነገሠበት የልማት ሥራ በማከናወን ላይ ነው፡፡ ይኽ የተገለጸው "በሰላም በፍትሕ- በልማት ጉዟችን" በሚለው ሥንኝ ነው፡፡ በሥንኙ የተጠሩት ሰላም፣ ፍትሕና ልማት ከሚገኙበት አነስተኛ ደረጃ ወደ ከፍተኛ በመሸጋገር ኺደት ላይ መኾናቸውን ጉዞ የሚለው ቃል ይገልጻል፡፡ መራመድን፣ መገስገሥን፣ ከአነስተኛ ወደ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ማድረግን፡፡ እንቅስቃሴው ሰላም፣ ፍትሕ እየሰፈነ መኾኑን፤ የልማት ሥራ መጀመሩን፤ ኹሉም በመዳበር ኺደት ላይ ናቸው ማለትን ይገልጻል፡፡ ሥንኙ እንደሚገልጸው ሰላምን የበለጠ ለማጽናት፣ ፍትሕን ለማጎልበት፣ ልማትን ለማዳበር የክልሉ ሕዝብ በተግባር እንቅስቃሴ ላይ ነው፡፡ ሰላም በሰፈነበት፣ ፍትሕ በነገሠበት ኹኔታ የልማት ሥራ በማከናወን ላይ ነው፡፡

በክልሉ መዝሙር "ተባብረን በሥራ፣ እንገነባሻለን" በሚለው ሥንኝ እንደተገለጸው፣ የክልሉ ሕዝቦች የወደፊት ተስፋ የተመሠረተው ሕዝቦቿ ተባብረው፣ አንድ ኾነው ክልላቸው እንድትበለጽግና እንድትለማ በማድረግ ላይ ነው፡፡ ይኽም በክልሉ የሚመጣው ለውጥ፣ ዕድገት፣ ብልጽግናና ልማት ዋነኛ ጥቅም ለክልሉ ሕዝቦች ነው ተብሎ እንዲታሰብ፣ እንዲታመን ያደርጋል፡፡ የክልሉ መዝሙር ዋነኛ ትኩረት በክልሉ ልማት ላይ በመኾኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለማምጣት ስለመቻሉ መዝሙሩ አያስተምርም፤ አይቀሰቅሰም፡፡ ይኽ ማለት ግን የዐማራ ክልል መልማት

[23] የመዝሙሩ ሥንኝ ሲተረጎም የተገለጸውን ማለት ይኹን እንጂ ክልሉ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ያለበትና ለረጅም ጊዜ የታረሰ በመኾኑ የመሬቱ ለምነት በአብዛኛው የተሟጠጠና የደን ሽፋኑም እጅግ የተመናነመ ነው፡፡ በዚኽም ምክንያት የክልሉ ነዋሪዎች ወደ ሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች እንዲሰፍሩ ተደርጓል፡፡

[24]ሕዝቦች የሚለው ብዙ ቁጥር አመልካች ቃል በቋንቋ፣ በባህል፣ በመልካ ምድራዊ አሠፋፈር፣ ኹለትና ከዚያ በላይ የኾኑ የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ፣ የየራሳቸው ባህልና የተለያየ መልክዓ-ምድራዊ አሰፋፈር ያላቸው የሰዎች ስብስብን ይገልጻል፡፡ በክልሉ ሕገ መንግሥት መግቢያ ላይ "እኛ የዐማራ ብሔራዊ ክልል ሕዝቦች" በማለት የተጠሩት በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 8 (1) "የአማራ ክልል ሕዝቦች የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ የበላይ ሥልጣን ባለቤቶች ናቸው፡፡" በሚለው ድንጋጌ የተጠሩትን ነው፡፡ የክልሉ ሕዝብ መዝሙር በክልሉ ለሚኖሩ ብሔር- ብሔረሰቦች ዕውቅና ይሰጣል፡፡ ነገር ግን በሕገ መንግሥት ዕውቅና ከተሰጣቸውና የራሳቸው የአስተዳደር መዋቅር ካላቸው ብሔረሰቦች ሌላ በክልሉ ሌሎች ሕዝቦችም ይኖራሉ፡፡ በክልሉ ሕገ መንግሥት በስም ያልተጠራው የአርጎባ ብሔረሰብ የልዩ ወረዳ አስተዳደር ተሰጥቶታል፡፡ በቅርቡም ለቅማንት ብሔረሰብ የራስ አስተዳደር ዕውቅና ተሰጥቷል፡፡ ይኽም በክልሉ ሕገ መንግሥት የክልሉ የሥልጣን ባለቤቶች ተብለው በክልሉ ሕገ መንግሥት የተጠሩት ብቻ አለመኾናቸውን ያስረዳል፡፡ "ሕዝቦችሽ" የሚለው ብዙ ቁጥር አመልካች ቃል የተጠሩት የዐማራ፣ የኽምራ፣ የአዊና የኦሮሞ ብሔር-ብሔረሰቦች ናቸው፡፡ የክልሉ ሕገ መንግሥት ሲጸድቅም፣ መዝሙሩ አገልግሎት እንዲሰጥ ሲወሰንም የአርጎባ ልዩ ወረዳና የቅማንት የራስ አስተዳደር ጥያቄዎች አልቀረቡም ነበር፡፡ ጥያቄ ያልቀረበባቸውንና ዕውቅና ያልተሰጣቸውን ራስን የማስተዳደር መብት የክልሉ መዝሙር ዕውቅና ይሰጣል ማለት አይቻልም፡፡ ስለኾነም "ሕዝቦች" በሚለው ብዙ ቁጥር አመልካች ቃል የተጠሩት በክልሉ ሕገ መንግሥት ዕውቅና የተሰጣቸው ብሔር-ብሔረሰቦች ናቸው ማለት ነው፡፡

ለአጎራባች ክልሎች በጠቅላላውም ለሀገር ጠቀሜታ አይኖረውም ማለት አይደለም፡፡ ልማትን በአንድ አካባቢ መጀመር የሀገር ዕድገት የመጀመሪያው ርምጃ ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል፡፡

ይኹን እንጂ በዚኽ ጥናት የክልሉ ልማት አልተመረመረም፡፡ ስለክልሉ ልማት ለመናገር በክልሉ የትምህርት ቤቶች መስፋፋትና በጥራት ትምህርት መስጠት፣ የጤና ተቋማት ግንባታና ተደራሽነት፣ የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ የክልሉን የመንገድ ልማት፣ የሙብራት አገልግሎት፣ የቴሌኮምዩኒኬሽን መስፋፋት፣ ማንነት የሚገለጽበት ባህልና ታሪክ ልማት ከሌሎች ክልሎች ጋር በማነጻጸር በጥናት ላይ ተመሥርቶ ማስረዳት አስፈላጊ ነበር፡፡ "የክልል ግብርና ለውጥና ዕድገትና የኢንዱስትሪ ልማት ምን ያኽል የክልሉን ሕዝብ ሕይወት እንደለመጠ ማስረዳት የክልሉ ሕገ መንግሥት ዓላማ መተግበሩን ወይም አለመተግበሩን መመስከር ያስችል ነበር፡፡ ይኽ አለመደረጉም በመዝሙሩ የተንፀባረቀውን ሐሳብ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

በአንቀጽ 5 (1) "በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ቋንቋዎች በመንግሥት ዘንድ እኩል እውቅና ይኖራቸዋል፡፡" በማለት የተደነገገው በክልሉ ውስጥ ለሚኖሩ ከአማርኛ የተለዩ ቋንቋዎችን ለሚናገሩ ብሔረሰቦች የተሰጠውን ዕውቅና ያስረዳል፡፡ የኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ኻምጣንኛና አማርኛ፣ እንዲኹም በአዊ ብሔረሰብ አስተዳደር አዊኛና አማርኛ የሥራ ቋንቋዎች ኾነው ያገለግላሉ፡፡ በአንቀጽ 5 (2) "አማርኛ የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ የሥራ ቋንቋ ይሆናል፡፡" በማለት በተደነገገው መሠረት በኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ኻምጣንኛና አማርኛ፣ እንዲኹም በአዊ ብሔረሰብ አስተዳደር አዊኛና አማርኛ የሥራ ቋንቋዎች ኾነው ያገለግላሉ፡፡ በኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ግን አማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ቢኖሩም የአማርኛ ቋንቋ ከኦሮምኛ ጋራ አገልግሎት አይሰጥም፡፡ በብሔረሰብ አስተዳደሩ በሚገኙ ከተሞች የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ቁጥር ከፍተኛ ቢኾንም የፍርድ ቤት ቋንቋ አፋን ኦሮሞ በመኾኑ ቋንቋቸውን መጠቀም አይችሉም፡፡ ለምሳሌ፣ አብዛኛው የባቲ ከተማ ነዋሪ የዐማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ቢኾንም የመንግሥት አገልግሎት መስጫ ተቋማት በኦሮምኛ ቋንቋ ብቻ በመኾኑ ነዋሪው ፍትሐዊ የኾነ አገልግሎት እንዳያገኝ አድርጎታል (ክብሮም፣ 2012)፡፡

የክልሉ ሕዝብ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋራ በመተባበር የውጭ ወራሪን ከተከላከለባቸው ታሪካዊ ክንዋኔዎች መካከል አንዱ ከጣልያን ወራሪ ጦር ጋራ ያደረገውን የዐርበኝነት ተጋድሎ የብሔረ ዐማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (1986፤ 6) የዐማራ "መላ ታሪኩ የአርበኝነትና የዴሞክራሲ ትግል ታሪክ ነው፡፡ የጣልያን ቅኝ አገዛዝ በአገሪቱ ላይ ለረጅም ጊዜ እንዳያንሰራፋ ከመጀመሪያው ጀምሮ ከፍተኛ ተጋድሎ በማድረግ ረገድ የዐማራው ሕዝብ ትግል አስተዋጽኦ በማበርከት ከሌሎች ኢትዮጵያውያን አጋሮቹ ጋራ ተሰልፎ አገራዊ ክብሩን አስጠብቋል፡፡" በማለት ይገልጻል፡፡ ይኹን እንጂ ይኽ ታሪክ በክልሉ መዝሙር እንዲንፀባረቅ በሕገ መንግሥቱ አልተደነገገም፡፡ በመዝሙሩ የዐማራ ሕዝብ "የታሪክ ማኅደር"[25] ነው መባሉ የሕዝቡን የዐርበኝነትና ጀግንነት

[25] ማኅደር የሚለው ቃል ዐውዳዊ ፍቺ በውስጡ ታሪክን የሚገልጹ ነገሮች የሚገኙበት ማለት ነው፡፡ ይኽም በክልሉ የሚገኙበትን የላሊበላና ሌሎች ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፣ የጎንደር ቤተመንግሥት፣ የጣና ገዳማት፣ ረጅም ዕድሜ ያስቆጠሩ መንፈሳዊ መጻሕፍት ማለት ነው ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፡፡ ስለኾነም፣ "የታሪክ ማኅደር" የሚለው የዐማራ ሕዝብ ሉዓላዊነትን ለማስከበር የከፈለውን መስዋዕትነትና የፈጸመውን የጀግንነት ተግባር በቀጥታ አይገልጽም፡፡ ለዚኽ ሐሳብ ማኀልበቻ የአመራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባህል ቢሮ በ2000 ዓ. ም. "የአማራ

ታሪክ አይገልጽም፡፡ ዐማራው ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በመተባበር የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለመጠበቅና ለማስከበር የከፈለውን መሥዋዕትነትና የጀግንነት ተግባር መፈጸሙን መዝሙሩ አያጸባርቅም፡፡ የክልሉ ሕዝብ በረጅም ዘመን ታሪኩ ሀገሩን ከወራሪ ጠላት ተከላክሎና ጠብቆ ያቆየ የመኾኑ ታሪክ በመዝሙሩ ቢንፀባረቅ ኖሮ ወጣቱ ትውልድ የአባቶቹን የጀግንነት ታሪክ እንዲያደንቅ፣ ባባቶቹ ታሪክ እንዲኮራ፣ ከእሱ የሚጠበቀውን ሀገርን ከጠላት የመጠበቅ ኃላፊነት ለመወጣት እንዲተጋ የሚያስችል ስሜት ለመፍጠር ይረዳ ነበር፡፡ ስለኾነም፣ የክልሉ ሕዝብ ታሪክ በክልሉ መዝሙር እንዲንጸባረቅ አለመደንገጉ ሕገ መንግሥታዊ ክፍተትም፣ የክልሉ መዝሙር ድክመትም ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

የዐማራ ሕዝብ በኢትዮጵያ የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት በተደረገው ትግል የነበረው ተሳትፎ በመዝሙሩ እንዲንጸባረቅ በክልሉ ሕገ መንግሥት አልተደነገገም፡፡[26] በኢትዮጵያ መንግሥት ሠራዊትና በኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ መካከል በተደረገው ጦርነት የዐማራ ሕዝብ የከፈለው መሥዋዕትነት ከፍተኛ ነበር (የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ፣ 1986፤ 6 -7)፡፡ በትጥቅ ትግሉ የተሳተፉት የዐማራው ጭቁን ሕዝብና "በክልሉ የሚገኙ ሌሎች የአናሳ ብሔረሰብ ሕዝቦችም" (ብአዴን፣ 1986፡ 8-9) ናቸው፡፡ ይኽ ታሪካዊ ክንዋኔ ቢኖርም በክልሉ መዝሙር የዐማራ ሕዝብ የትግል ታሪክ ያለመደንገጉ ምክንያት፣ አንድም፣ የዐማራ ሕዝብ ለለውጡ ያደረገው አስተዋጽኦ የለም ወይም ዝቅተኛ ነው ብሎ በማመን ነው፡፡ አንድም፣ በኢትዮጵያ ለመጣው ለውጥ የዐማራ ሕዝብ ያደረገውን አስተዋጽኦ አለመግለጽ የሕዝቡ ሥነ ልቦና ከፍ እንዳይልና እንዳይኅሉብት ለማድረግ ያስችላል ብሎ በማሰብ ኾን ብሎ  በመተው ነው፡፡ አንድም፣ የዐማራ ሕዝብ ከትግራይ ሕዝብ ጋራ የሚወዳደር የትግል ታሪክ የለውም ብሎ በማሰብና የዐማራ ሕዝብ ለውጥ እንዲመጣ ያደረገውን ትግል በክልሉ ሕገ መንግሥት መደንገግ "የበለጠ ታግሏል" ከሚሉት ትሕነግና የትግራይ ሕዝብ ጋራ እኩል ሥነ ልቦናዊ ስሜት እንዳይፈጥር ለማድረግ ታስቦ ነው፡፡ አንድም፣ በመዘንጋቱ ሊኾን ይችላል፡፡ ከኹሉም በላይ ግን የትግሉ ውጤት ለዐማራ ሕዝብ ምን አስገኝቷል? የሚለው ጥያቄ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ኢሕዴን/ብአዴን በዐማራ ሕዝብ ላይ የተፈጸመውንየሰብአዊና የዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥሰት ለማስቆም ያደረገው ጥረት የለም ወይም እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡ እነዚኽ መብቶች ባልተከበሩበት ኹኔታ የዐማራው ሰፊ ሕዝብና በክልሉ የሚኖሩ ብሔረሰቦች የደርግን መንግሥት ከሥልጣን ለማስወገድ በተደረገው ትግል ስለአደረጉት የትግል ተሳትፎ በመዝሙሩ መግለጽ የሚፈይደው ቁምነገር ይኖራል ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡ ይኽም ኾኖ የክልሉ መዝሙር በዐዋጅ ባለመጽደቁ፣ የት? መቼ? እንዴት?

---

ሕዝብ ታሪክ፣ ባህልና ቋንቋ" በሚል ርእስ ያዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ ተካቶ የነበረው 84 ገጾች የታሪክ ክፍል እንዲቀር ተደርጎ "የአማራ ሕዝብ ባህልና ቋንቋ" በሚል ርእስ በ2001 ዓ. ም. እንዲታተም መደረጉ ነው፡፡ የተዘጋጀው መጽሐፍ የታሪክ ክፍሉ እንዲወጣ የተደረገው  በታሪክ ባለሙያ ተገምግሞ ተቀባይነት ካገኘና ወደ ማተሚያ ቤት ለመላክ የዋጋ መጠየቂያ ቀጽ ከተሰበሰበ በኋላ ነው፡፡

[26] ይኽንን የምንመለከተው በትግሉ የተገኘው  የሥርዓት ለውጥ ያስገኘውን አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት በመገምገም አይደለም፡፡ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት  ስለክልሉ መዝሙር ከተደነገገው ጋር በማነጻጸር ነው፡፡ ስለኾነም፣ ተሻሽሎ የወጣውን የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት ለማፅደቅ በወጣው አዋጅ ቁጥር 45/1994 አንቀጽ 4 የትግራይ ብሔራዊ ክልል  መዝሙር የትግራይን ሕዝብ "የትግል ታሪክ" እንዲያንፀባርቅ ተደንግጓል፡፡ ይኽ ዓይነት ድንጋጌ በዐማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ስለክልሉ መዝሙር በተደነገገው እንዲካተት አልተደረገም፡፡

እንደሚዘመር የአፈጻጸም መመሪያ ባለመውጣቱ የአጠቃቀም ችግር ይስተዋላል። አንዳንድ ቦታ ብሔራዊ መዝሙሩን በማስቀደም የክልሉን መዝሙር ቀጥለው ይዘምራሉ፡፡ እንዲኹም አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ደግሞ ጠዋት ብሔራዊ መዝሙሩን፣ ምሽት ደግሞ የክልሉን መዝሙር ይዘምራሉ፡፡[27] ከዛም አልፎ በክልሉ መዝሙር ውስጥ "የዐማራነትን ክብር፣ ደማቅ ዐርማ ይዘን" የሚል ሥንኝ ስለተካተተ የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ተማሪዎች "ማንነታችንን ትተን ለዐማራነት ክብር አንዘምርም" በማለታቸው የክልሉን መዝሙር አይዘምሩም፡፡[28] ይኸም መዝሙሩ በክልሉ ብሔረሰቦች ተቀባይነት እንደሌለው አመላካች ነው፡፡

### 3) መደምደሚያ

የዐማራን ክልል መዝሙር ለመድረስ ያነሣሡ ታሪካዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶች ተመርምረዋል፤ ከላይ ከቀረቡት ማስረጃዎች ለመገንዘብ የሚቻለው ኢሕዴን ለዐማራው ሕዝብ በግንባር ቀደምነት ለመታገል የተንቀሳቀሰው ጠባቦችንና ትምክህተኞችን ለመታገል ነው፡፡ ጠባቦች የሚባሉት "በስሕተት" የዐማራውን ሕዝብ ጨቋኛቸውና በዳያቸው አድርገው የሚቆጥሩ የሌሎች ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የፖለቲካ ተወካዮች ናቸው፡፡ ዐማራ የሚባል ሕዝብ መኖሩን አምኖ "የሚሚገትለት የራሱ የፖለቲካ ድርጅት ስለሌለው በሌሎች ተጠቃ" የሚለው አመለካከት ደግሞ ሰፊውን የዐማራ ሕዝብም ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋራ የሚያጋጭ ነው ብሎ በማመን ኢሕዴን ለዐማራው ሕዝብ መታገሉን ይገልጻል፡፡ ይኸ የኅብረተሰብ ክፍል ዐማራ ነው፡ ፡ እንደ ኢሕዴን እምነት የትምክህት አመለካከት "የሰፊውን የዐማራ ሕዝብ" ጥቅም ይጎዳል በማለት የታገለው "ትምክህተኛ አመለካከት ያራምዳል" ያለውን የዐማራ የህብረተሰብ ክፍል ነው ፡፡

የዐማራ ክልል መዝሙር የተደረሰውና አገልግሎት መስጠት የጀመረው በ1989 ዓ. ም. ነው፡፡ ለመዝሙሩ ግጥምና ዜማ (ኖታ) በማቅረብ ባለሙያዎች እንዲወዳደሩ በማስታወቂያ የጋበዘው፣ ለውድድር የቀረቡትን ሥራዎች ገምጋሚ የመደበው፣ መዝሙሩ ምን ምን ጉዳዮችን ማንጸባረቅ እንዳለበት በክልሉ ሕገ መንግሥት የደነገገው የብሔረ ዐማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ነው፡፡ የክልሉ መዝሙር የሚያንጸባረቀው ክልሉን በበላይንት የሚመራው የፖለቲካ ድርጀት የፖለቲካ ማራመጃ ሐሳቦችን ነው፡፡ ይኹን እንጂ መዝሙሩ እንዴትና መቼ እንደሚዘመር በሕግ አልተደነገገም፤ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያም አልወጣለትም፡፡ በዚኽም ምክንያት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ብሔራዊ መዝሙር ጠዋት በትምህርት ቤቶች ሲዘመር የክልሉ መዝሙር በአንድ ዓይነት ቅደም ተከተል አይዘመርም፡፡ ይኸውም በየክልሉ ትምህርት ቤቶች ጠዋት የዐማራ ክልል ሰንደቅ ዓላማም፣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሰንደቅ ዓላማም ሰንደቃቸው ላይ ሲሰቀሉ አንዳንድ ቦታ ቀድሞ የክልሉ መዝሙር ሲዘመር፣ ምሽት ሰንደቅ ዓላማዎቹ ሲወርዱ ደግሞ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ብሔራዊ መዝሙር ይዘመራል፡፡ አንዳንድ ቦታ ደግሞ ጠዋት የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር ምሽት ደግሞ የክልሉ መዝሙር እንዲዘመር ይደረጋል፡፡ ኹለቱም መዝሙሮች ጠዋት

[27] ወ/ሮ ስለእናት ይብሬ፣ ደሴ ቦሩ ሜዳ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 20 ቀን 2013 ዓ. ም.፡፡
[28] ወይዘሮ አሰግድ ሚሪሳ፣ ቃለ መጠይቅ፡፡

የሚዘመሩባቸው ትምህርት ቤቶችም በየተራ የሚዘመሩባቸው ትምህርት ቤቶች እንዳሉ ለመረዳት ተችሏል፡፡

የክልሉ መዝሙር የዐማራን ብሔር በክልሉ ከሚገኙ ሌሎች ብሔረሰቦች ማለትም ከኽምራ፣ ከአዊና ከኦሮሞ ብሔረሰቦች ያስበልጣል፡፡ የዐማራን ክብር ከፍ አድርጎ ሲሰብክ የክልሉን ብሔራሰቦች እኩልነት በተገቢው ደረጃ አያንፀባርቅም፡፡ ከዚኽም በላይ ብሔረሰቦች በየትምህርት ቤቶቻቸው የክልሉን መዝሙር ሲዘምሩ የራሳቸውን ማንነት ትተው የዐማራን ክብር ከፍ ስለማድረግ እንዲሰብኩ ይጠይቃል፡፡ ይኽም በክልሉ ባሉት ብሔረሰቦች ዘንድ ቅሬታን ፈጥሯል፡ ፡ ኾኖም በኽምራና በአዊ ብሔረሰቦች በሚገኙ ትማህርት ቤቶች ቅሬታቸውን እንዳለ ኾኖ መዝሙሩን አኹንም መዘመራቸውን ቀጥለዋል፡፡ በኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደር ግን የኦሮሞ ልጅ ቆሞ የራሱን ትቶ የዐማራን ክብር አይሰብክም በማለት በትምህርት ቤቶቻቸው የክልሉን መዝሙር እንዲዘመር አያደርጉም፡፡ ይኽም የክልሉ መዝሙር አገልግሎት በሚሰጥባቸው ቦታዎች መዝሙሩን "የእኛ ነው" የሚል ስምምነት እንደሌለ ማስረጃ ነው፡፡ መዝሙሩ የዐማራ ክልል ሕዝብ ለሥራ የተጋ፣ የታሪክ፣ የአኩሪ ባህልና የድንግል መሬት ባለቤት እንደኾነ ቢገልጽም ለክልሉ ሕዝብ እኩል ኩራትን፣ በራስ መተማመንን አይፈጥርም፡፡ የክልሉ ብሔር-ብሔረሰበቦች መዝሙሩን በ"የእኛነት" ስሜት እንዲዘምሩት አያደርግም፡፡

የዐማራ ክልል ብሔረሰቦች በመዝሙሩ የተንፀባረቀውን መልእክት እንዲጋሩ አለመደረጉ የመዝሙሩ ድክመት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ስለኾነም በመዝሙሩ የተንጸባረቀው የክልሉን ብሔረሰቦች ክብር የሚቀንሰውን ይዘት ማስተካከል ተገቢ ነው፡፡ "የአማራነትን ክብር - ደማቅ አርማ ይዘን" የሚለው የመዝሙሩን ሥንኝ የኢትዮጵያዊነትን ክብር - ደማቅ አርማ ይዘን በሚል ወይም በሌላ ሥንኝ ሙተካት የመዝሙሩን አግላይ ይዘት መለወጥ ያስችላል፡፡

የዐማራ ክልል መዝሙር ከኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ጋራ በመከባበር፣ በእኩልነት፣ በፍቅር፣ በአንድነት አብሮ ስለመኖር መስበኩ ጠንካራ ጎኑ ተደርጎ ሊታይ ይችላል፡፡ በዚኽም የክልሉ ታዳጊዎች ከኢትዮጵያውያን ጋራ እንዴት መኖር እንደሚገባቸው በክልሉ መዝሙር እንዲገነዘቡ ማስተማር ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ለመፍጠር አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ይኹን እንጂ በተለያዩ ክልሎች የሚኖረው ዐማራ በዘሩ ተለይቶ እየተገደለ፣ አካሉን እያጣ፣ ንብረቱን እየተቀማ፣ ከሚኖርበት እየተፈናቀለና እየተሰደደ በሚገኝበት ነባራዊ ኹኔታ በመዝሙር ስብከት አንድነትን ማጠናከር አይቻልም፡፡ ዐማራው በሚኖርባቸው ክልሎች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቹ ሳይከበሩ በሌሎች ክልሎች ከሚኖሩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጋር ተከባብሮ እንደሚኖር ተደርጎ በመዝሙሩ መንፀባረቁ በዘማሪዎቹ ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

በመዝሙሩ የሚንጸባረቀው ይዘት ምንም መልካም ቢኾን በሀገሪቱ የሕግ የበላይነት ካልሰፈነ፣ የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት በተሟላ መልኩ ካልተከበረ፣ ዜጎች በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ተዘዋውሮ የመሥራት፣ ንብረት የማፍራትና የመኖር መብታቸው በተሟላ መልኩ ካልተከበረ በዐማራ ክልል መዝሙር ይዘት ፍቅርን፣ እኩልነትን፣ አንድነትን ቢሰብክም ውጤት

አያመጣም፡፡ መዝሙሩ በሀገሪቱ የሚፈጸመውን መልካም ተግባር የሚያግዝ እንጂ ብቻውን መልካም ውጤት አያስገኝም፡፡ በኢትዮጵያ የሕግ የበላይነትን ማስፈን፣ የዜጎችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ማክበር የዐማራ ክልል መዝሙር ትውልድን በመልካም ብሔራዊ ፍቅርና የኃላፊነት ስሜት ለመቅረጽ ይረዳል፡፡

ከዚኽ በላይ እንደተገለጸው፣ የዐማራ ክልል መዝሙር፣ የክልሉን ሕገ መንግሥት ዓላማዎች፣ የዐማራ ሕዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋራ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብሮ ለመኖር ያለው እምነትና የወደፊት የጋራ ዕድሉ የሚሉት ተንጸባርቋል፡፡ ከነዚኽ በክልሉ ሕገ መንግሥት ከተደነገጉትና በመዝሙሩ ከተንጸባረቁት ሦስት ይዘቶች በተጨማሪ የሕዝቡ የቀደመ ታሪክና በትጥቅ ትግሉ ወቅት የነበረው ተሳትፎ በመዝሙሩ የትግል ታሪክ መንጸባረቅ ነበረባቸው፡፡

## መረጃ ጽሑፎች


ሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት፡፡ 1997፡፡ *የሐረሪ ሕዝብ ክልል የተሻሻለው ሕገ-መንግሥት፤ ሐረር ነጋሪት ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 46/1997*፡፡ 9ኛ ዓመት፣ ቁጥር አንድ፡፡

ሕገ መንግሥት ኮሚሽን፡፡ 1986፡፡ "ስለ ሕገ መንግሥት መሠረተ ሐሳቦች ለሕዝብ ውይይትየቀረበ ጽሑፍ ቁጥር 1"፡፡ አዲስ አበባ (ተባዝቶ የተጠረዘ)፡፡

ሙሉቀን ተስፋው፡፡ 2008፡፡ *የጥፋት ዘመን፣ ከ1983 እስከ 2007 ዓ. ም. በዐማራ ሕዝብ ላይ ተፈጸመ ዘር ማጽዳት* ፡፡ አዲስ አበባ፤ (ማተሚያ ቤቱ አልተገለጸም)፡፡

ሶማሌ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት፡፡ 1994፡፡ *የተሻሻለው የሱማሌ ክልል ህገ- መንግስት በሥራ ላይ መዋሉን ለማሳወቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፰ሀ፲፱፻፺፬*፡፡

በአካል ንጉሤ፡፡ 2011፡፡ "የራያ ባህላዊ ማንነትና አስተዳደራዊ ጥያቄዎች የዘገየ ፍትሕ እንደተጓደለ ይቆጠራል"፡፡ በረራ 1ኛ ዓመት፣ ቁጥር 14 መጋቢት 12 ቀን፣ 2011፣ ገጽ 21፡፡

ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት፡፡ 1995፡፡ *የተሻሻለው የቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት፤ ልሣነ-ሕግ ጋዜጣ አዋጅ ቁጥር 31/1995*፡፡ ስምንተኛ ዓመት፣ ቁጥር 4፡፡

.............፡፡ 1995፡፡ *አዋጅ ቁጥር 1/1988 የቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት አዋጅ፤ የቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ልሣነ-ሕግ ጋዜጣ*፡ 1ኛ ዓመት፣ ቁጥር 1፡፡

ብሔራዊ መዝሙር ዝግጅት ኰሚቴ፡፡ "ለኢትዮጵያ ሽግግር መንግሥት ተወካዮች ምክር ቤት ያቀረበው ማስታወሻ"፤ ሰኔ 2 ቀን 1984፡፡

ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን)፡፡ 1998፡፡ *ፅናት፤ በታይ ሰማእታት ገድልና በታታሪው የአማራ ህዝብ ፅናት የታጀበው የብአዴን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ጉዞ ከ1983-1997 ዓ. ም፡፡* ቅፅ ፪፤ 25ኛውን ዓመት የብአዴን ምስረታ ምክንያት በማድር የተዘጋጀ (የታተመበት ቦታና ማተሚያ ቤቱ አልተገለጸም)፡፡

ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ፡፡ 1986፡፡ *የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) ፕሮግራም*፡ ዐዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት፡፡ 2008፡፡ *የኢህዴን-ብአዴን ታሪክ 1973 - 2008*፡፡ (የታተመበት ቦታ አልተገለጸም) Mega Printing P.L.C.

አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ፡፡ 2002፡፡ *የአማራ ሕዝብ ባህልና ቋንቋ*፡ ባሕር ዳር፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ፡፡ 2002፡፡*"የአማራ ሕዝብ፣ ባህልና ቋንቋ፡፡"* ባሕር ዳር (ያልታተመ)፡፡

ትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት፡፡ 1968፡፡ *መግለጫ* (ት.ህ. ነ. ኣ. ድ) የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ድርጅት፡፡ የመጀመሪያ እትም፤ Retrived at: https: www. Satenaw.com/https-www-satenaw-com-wp-content-uploads 2017, accessed on 5 May 2019.

ትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፡፡ 1994፡፡ *ተሻሽሎ የወጣውን የትግራይን ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር 45/1994*፡፡ 10ኛ ዓመት ቁጥር 2፡፡

ቹቹ አለባቸው፡፡2011፡፡ *ዳገት ያበረታው የአማራው ፍኖት*፡፡ ባሕር ዳር፤ ብራና መጻሕፍት ቤት፡፡

አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት፡፡ "አዋጅ ቁጥር 59/1994 የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ-መንግሥት ማፅደቂያ አዋጅ፡፡" *የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ዝክረ ሕገ* ፡፡

አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጉባዔ፡፡ "ምጥን ቃለ ጉባዔዎች 1987- 1992፡፡" ባሕር ዳር (ያልታተመ)፡፡

አማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት፡፡ "አማራ ብሔራዊ ክልል መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ 1985– 1992፡፡" ባሕር ዳር (ያልታተመ)፡፡

አፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት፡፡ "የተሻሻለው የ1994 ዓ. ም. የአፋር ክልል ሕገ መንግሥት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር 14/1994፤" *የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ*፡ 3ኛ ዓመት፣ ቁጥር 1፣ ሰኔ 28/1994፡፡

ኢትዮጵያ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ጉባዔ፣ "የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር"፣ *ነጋሪት ጋዜጣ* ፣ አምስተኛ ዓመት፣ ቁጥር 1፣ ሐምሌ 15 ቀን 1983፡፡

ኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የተወካዮች ምክር ቤት 70ኛ መደበኛ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ፣ ግንቦት 3 ቀን፣ 1985፡፡

ኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የተወካዮች ምክር ቤት 33ኛ መደበኛ ስብሰባ ቃለ ጉባዔ፣ ጥር 28 እና 30፣ 1984፡፡

ኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣ፡፡ "ብሔራዊ ክልላዊ የሽግግር መስተዳድሮች ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 7/1984፡፡" ኢትዮጵ የሽግግር መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣ፡፡

ኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የተወካዮች ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ፡፡ አዋጅ ቁጥር 7/1984 ብሔራዊ ክልላዊ የሽግግር መስተዳድሮችን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ፣ *የኢትዮጵያ የሽሽግር መንግሥት ነጋሪት ጋዜጣ* ፡፡

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፡፡ "የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ለማጠናከርና ሥልጣንና ተግባሩን ለመዘርዘር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፪፻፶፩/፲፱፻፺፫፡፡" *ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ* ፡፡

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፡፡ "የፌዴራሉ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አዋጅ ቁጥር ፪፻፶/፲፱፻፺፫፡፡" *ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ* ፡፡

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አዋጅ ቁጥር ፩/፲፱፻፹፯፡፡ *ፌዴራል ጋሪት ጋዜጣ* ፡፡

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ፡፡ የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፬፻፲፮/፲፱፻፺፮፡፡ *የኢትዮጵያ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ*፡

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፬/፪ሺ፪፡፡ *ፌዴራል ጋሪት ጋዜጣ፡፡*

ክብሮም አሰፋ፡፡ 2012፡፡ "የፌዴራል የሥራ ቋንቋን ከማብዛት በፊት"፣ *ፍትሕ፡፡ አንደኛ ዓመት*፣ ቁጥር 45፣ (መስከረም)፣ ገጽ 14-16፡፡

ገብሩ አስራት፡፡2007፡፡*ሉዓላዊነትና ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ*፡ አዲስ አበባ (ማተሚያ ቤቱ አልተገለጸም)፡፡

ገብሬ ብዙነህ። 2010፡፡ *የአዊኛና አማርኛ ቋንቋዎች ንጽጽራዊ ትንተና (አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለመማር/ለማስተማር* (ገብሬ ብዙነህ)። አዲስ አበባ፤ ኤኤም ማተሚያና ማሸጊያ ኃ/የተ/የግ/ ማኅበር፡፡

Butz, David A. 2009. "National Symbols as Agents of Psychological and Social Change." In፡ *Poltical Psychology*. 30(5) Pp. 779-804.

Daughtry, J. Martin. 2003. "Russia's New Anthem and the Negotiation of National Identity." In: *Ethnomusicology*. 47 (1), Pp. 42-67.

Office of Population and Housing Census Commission Central Statistical Authority. 1999. *The 1994 Population and Housing Census of Ethiopia Results for Benishangul-Gumuz Region Volume II Analytical Report*. Addis Ababa.

Office of Population and Housing Census Commission Central Statistical Authority. 1999. *The 1994 Population and Housing Census of Ethiopia Results for Harari Region Volume II Analytical Report*. Addis Ababa.

Office of Population and Housing Census Commission Central Statistical Authority.1998. *The 1994 Population and Housing Census of Ethiopia Results for Tigray Region Volume II Analytical Report*. Addis Ababa.